የማንነት ፖለቲካ ምንነትና አደጋዎቹ
ገጽ 10

አማራንና ኦርቶዶክስን እንደ አውሬ...
ገጽ 8

የደም ካባ
ገጽ 13

በሆሳዕና የመስቀል በዓል እንዳይከበር ሀገረ ስብከቱ ከለከለ
ገጽ 4

# ባልደራስ



ፖለቲካና ሴትነት

1ኛ ዓመት ቁጥር 02 መስከረም 19 ቀን 2013 ዓ.ም.



# አሸባሪው መንግሥት ወይስ እስክንድር?

# ለኢትዮጵያ ሰላምና አንድነት በትብብር መሥራት ይገባል

በአሁን ወቅት ጽንፈኛ ብሔርተኛ ኃይሎች እየተስተዋሉ ናቸው:: እነዚህ ኃይሎች በተደጋጋሚ የኢትዮጵያን አንድነት፣ መገለጫ እሴቶቿን ብሎም ኢትዮጵያዊነትን የማፈራረስ እንቅስቃሴዎች ሲፈጽሙ ይታያሉ:: ሆኖም ሰሜን እና ደቡብ ንፍቀ ክበባት ላይ የተንቆራጠጡ የሁሉም የፖለቲካ አስተሳሰቦች የሚቀጥሉት ኢትዮጵያ እንደ አገር ስትቀጥል መሆኑን መገንዘብ ይኖርባቸዋል ለዚህም ሁሉንም አስተያየቶች ወደ አንድ የጠረጴዛ ውይይት በማምጣት መፍትሔ መፈለግ ይገባል:: ኢትዮጵያን ከገባችበት የማያስፈልግ የፖለቲካ ውጥንቅጥ ለማውጣትም በሕብረት መሥራቱ እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው::

ከዚህ አንፃር ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ (ባልደራስ) እና የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) የካቲት 29 ቀን 2012 ዓ.ም. በጋራ ለመሥራት የፈጠሩት ቅንጅት የሚበረታታ ነው:: የባልደራስ- መኢአድ ቅንጅት ተመስርቶ ይፋ በተደረገ ማግሥት የኮሮና ተህዋሲ ወረርሽን ያስከተለውን የመሰብሰብ ገደብ ተከትሎ የነበሩ ጎታች መንስኤዎች በአሁኑ ወቅት በመቀነሳቸው በመጭዎቹ ጊዜያት ቅንጅቱ በተሻለ ጥራትና ፍጥነት ሥራዎቹን ሊቀጥል ይገባል::

ቅንጅቱ ከሰሞኑ ለሌሎች የፖለቲካ ተቋማትም ጭምር ያቀረበው ጥሪ እጅግ የሚበረታታና ወደ አንድ አገራዊ መግባባት ሊወስድ የሚችል ፍኖት ነው:: ‹‹በሀገራችን ያለውን ሰፊ የፖለቲካና የልሂቃን ክፍፍል በማጥበብ በሚመጣው ምርጫ ላይ ተቀናጅቶ በመወዳደር አብላጫውን የሕዝብ ድምፅ ይዞ መንግሥት መመሥረት ዓላማ ቅድሚያ ተሰጥቶታል። ይህም ኢትዮጵያ አንድነቷና ሕብረቷ ተጠብቆ እንዲኖር ለማድረግና ከፍተኛ የሆኑ መዋቅራዊ ችግሮችን ለመፍታት እንዲሁም ሀገሪቱ በሰላምና በእውነተኛ የልማት ጎዳና ከፍ ብላ እንድትጓዝ ለማስቻል ያለመ ነው›› ብሏል የሁለቱ ፓርቲዎች ቅንጅት ዓላማ::

በመሆኑም ይህንን ዓላማ የሚጋሩ የፖለቲካ ተቋማት ሁሉ የቅንጅቱ አባል በመሆን አብረው ሊሠሩ እንደሚገባ የባልደራስ - መኢአድ ጥምረት ጥሪ አቅርቧል:: የቅንጅቱ አባል ለመሆን ጥያቄ ያቀረቡ የፖለቲካ ፓርቲዎችን እንደሚያወያይና ጥያቄያቸውንም ተቀብሎ ወደ አባልነት በማስገባት ቅንጅቱን እንደሚያሰፋ ከሰሞኑ በሰጠው መግለጫ ጠቁሟል::

ባልደራስ በቅርቡ ያስጀመረውን የአዲስ አበባ የራስ ገዝ አስተዳደር ወይም በወቅቱ የፌዴራሊዝም አጠራር የ‹ክልልነት› ጥያቄም አቻ የፖለቲካ ተቋማት እንዲደግፉትና ሁሉም ነዋሪዎቿ በብሔር ሳይለያዩ ባለመብት የሆኑባት አዲስ አበባን ለመፍጠር እንዲያግዙት ጥሪ ማቅረቡ የሚበረታታ አጀንዳ ነው:: ከተማዋ የሁሉም ኢትዮጵያውያን እንደመሆኗ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ለከተማዋ ህልውና እና ዕድገት በጋራ ሊሠሩ ይገባል:: በተለይም የገዥው ፓርቲ አመራሮች የአዲስ አበባን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥሉ ንግግሮችን በአደባባይ ሲናገሩ እንደ ሙዚቃ በንግግራቸው መዝናናት ወይም ሰምቶ ዝም ማለት ተገቢ አይደለም:: ንግግሩ ከእኩይ አስተሳሰብ የሚመነጭ በመሆኑ በጋራ መታገል ያስፈልጋል:: አዲስ አበባ የአገሪቱ የፖለቲካ ማዕከል እንደመሆኗ ይህ ልዩ ትኩረት መስጠት ያሻል:: በመሆኑም ባልደራስ ያስጀመረውን ይህንን ግዙፍ አጀንዳ ለመደገፍ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሊነሱ ይገባል::

በፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤትም ሆነ በጠቅላይ ሚንስትሩ ሰብሳቢነት የሚደረጉ የፓርቲዎች የጋራ ስብሰባዎች ሁሉንም አሳታፊ ሊሆኑ ይገባል:: ገዥው ፓርቲ የራሱ ‹ታፔላ› የሆኑ የተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችን ሰብስቦ ‹አወያየሁ› ከሚለው በፍርሀትና በጠላትነት የታጀበ ልማዱ መላቀቅ ይኖርበታል:: ብሔራዊ መግባባትም ሆነ አገራዊ አንድነት የሚመጣው በአንድ አዳራሽ ውስጥ እንደ አንድ ሰው ተመሳስለው በተለያዩ ወንበሮች የተቀመጡ ሰዎችን ሰብስቦ በማስጨብጨብ አይደለም፤ የተለያዩ ሀሳቦችና አመለካከት ያላቸውን ሰዎች እንዲቀራረቡ በማድረግ እንጂ:: ስለዚህ ለኢትዮጵያ ሰላምና አንድነትን ለማምጣት ሁሉም በጋራ መሥራትና መወያየት የግድ ይለዋል።

**ባልደራስ ጋዜጣ**
መስከረም 1 ቀን 2013 ዓ.ም.
ተመሰረተ

በየ15 ቀኑ የሚታተም

**አሳታሚ**
ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ
ፓርቲ (ባልደራስ)

**ዋና አዘጋጅ**
ጌጥዬ ያለው
ክፍለ ከተማ:- ቂርቆስ
ወረዳ:- 02 የቤት ቁጥር:- አዲስ
ስልክ:- +2519 24 51 70 77
ኢ-ሜይል:- newsgett@gmail.com

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
ወግደረስ ጤናው

**አምደኞች**
ገለታው ዘለቀ
ኢንጂነር ጌታነህ ባልቻ

**አርታዒ**
መሰበወርቅ ቅጣው
ነብዩ ውብሸት

**ፅሐፊ:-** ሕይወት ዳዊት

**የገፆች ቅንብር** ሐብ-ዲዛይን

**ገፀ ድር አስተዳደር** ኢስያስ ፅጉ

# አማሮች ወደ አዲስ አበባ እንዳይገቡ የኦሮሚያ ፖሊስ ከለከለ

ከተለያዩ የአማራ ‹ክልል› አካባቢዎች ወደ አዲስ አበባ በአውቶብስ እየተጓዙ የነበሩ መንገደኞችን የኦሮሚያ ፖሊስ ዓባይን ተሻግረው ገብረ ጉራቻ ከተማ እንደደረሱ ወደ አዲስ አበባ እንዳይገቡ አግቷቸዋል። ከተሽከርካሪ ወርደው በእግር ወደ ከተማዋ እንዳገቡ በሚልም ፖሊስ አውቶብሶች ውስጥ በመግባት ዓባይን አሻግሮ እስከ ደጀን ከተማ ድረስ ወደ መጡበት መልሷቸዋል። ድርጊቱ የተፈፀመው መታወቂያቸውን በማንበብ ሲሆን ከተሳፋሪዎች መካከል የአማራ ተወላጆች ብቻ ተለይተው ወደ አዲስ አበባ እንዳገቡ መከልከላቸውን መንገደኞች ለባልደራስ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል በስልክ ገልፀዋል። ተንቀሳቃሽ ስልኮቻቸውን በፖሊስ በመነጠቃቸው ደጀን ከተማ ውስጥ በሚኖሩ ሌሎች ሰዎች ስልክ ለአስቸኳይ ጉዳዮች በተውሶ እየተጠቀሙ እንደሆነም ተናግረዋል። ተጓዦቹ በከፊል የዘመን መለወጫ ወይም የእንቁጣጣሽ በዓልን በትውልድ ቀያቸው አክብረው ወደ ቋሚ መኖሪያቸው አዲስ አበባ እየተመለሱ እንደነበር ጠቁመዋል። ከፊሎች ደግሞ በኤርትራ በረሃ ሕወሓት/ኢሕአዴግን ሲታገሉ የነበሩ አርበኞች እንደሆኑ ከደጀን የደረሱን መረጃዎች ያመላክታሉ።



የኦሮሚያ ፖሊሶች ወደ መጡበት ሲመልሷቸው ግን ‹‹የአዲስ አበባን የሕዝብ ስብጥር ለመቀየር ነው የምትሄዱት። የመስቀል በዓልን በአዲስ አበባ ለማክበር ነው የምትሄዱት። ከዚህ በኋላ መስቀል በአዲስ አበባ አይከበርም። ስለዚህ ማለፍ አይቻልም›› እንዳሏቸው ተናግረዋል። ከተጓዦች መካከል ለሕክምና ወደ አዲስ አበባ የሚመጡ እና የውጭ ሀገር የጉዞ ቀጠሮ የነበራቸው ይገኙበታል። ለምን እንደሚከለከሉ የጠየቁ መንገደኞች በኦሮሚያ ልዩ ፖሊስ ተደብድበዋል።

መንገደኞችን ያለማሳለፍ እንቅስቃሴው ላለፉት ስምንት ቀናት ቀጥሏል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከወራት በፊት ከ2 መቶ በላይ የአማራው ሕዝብ ተወላጅ የጉልበት ሠራተኞችን እና የጎዳና ላይ ተዳዳሪዎች በሌሊት በአውቶብስ አሳፍሮ በመውሰድ ባሕር ዳር ከተማ በትኗቸው መምጣቱ የሚታወስ ነው። በወቅቱ የተሰጠው ምክንያት በጎዳና ላይ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ የኮሮና ተህዋሲን ለማባባስ ምክንያት ነው የሚል ነበር።

# እነእስክንድር ነጋ በቤተሰቦቻቸው እንዲጠየቁ ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ ፖሊስ አልተቀበለም



መንግሥትን በኃይል ለመገልበጥ ሞክረዋል በሚል የሽብር ክስ ምክንያት በቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ የሚገኙት የባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ (ባልደራስ) አመራሮች ማለትም እስክንድር ነጋ፣ ስንታየሁ ቸኮል፣ አስቴር ስዩም፣ አስካለ ደምሌ እና ሌሎችም በቤተሰቦቻቸው እንዲጠየቁ ፍርድ ቤቱ ባለፈው ማክሰኞ መስከም 12 ቀን 2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት አዟል። ይሁን እንጂ ይህ ዜና እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ እስረኞችን መጠየቅ እንዳልቻሉ ቤተሰቦቻቸው ገልጸዋል። በተለይም ወይዘሮ አስቴር ስዩም ቤተሰብ እያመላለሰላቸው አራስ ልጃቸውን ጡት ማጥባት እንዲፈቀድላቸው ቢጠይቁም የፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ አልተፈፀመም።

ዐቃቤ ሕግ ክሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ ፍርድ ቤት ለመጭው መስከረም 19 ቀን 2013 ዓ.ም. ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል። ተፈፀመ ያለው ወንጀል በትክክል የትኛው የአዲስ አበባ ሥፍራ ላይ፣ መቼና በስንት ሰዓት ብሎም ከሰባቱ ተከሳሾች በማን እንደተፈፀመ ተጨባጭ ማስረጃ እንዲያቀርብም ታዟል። ‹‹ሰባተኛ ተከሳሽ በተለያዩ ስሞች ይጠቀማሉ፤ ከዚህ በፊት ከማረሚያ ቤት ያመለጡም ናቸው›› ሲል ዐቃቤ ሕግ ላቀረበው ክስ ከማረሚያ ቤቱ ሲያመልጡ በየትኛው ስም ተመዝግበው እንደነበርና አሁን የተከሰሱበት ስም ስለመሆን አለመሆኑ አቶ እስክንድር ነጋ ደጋግመው ቢጠይቁም ዐቃቤ ሕጉም ሆኑ ዳኞች ምላሽ ከመስጠት ተቆጥበዋል። ይሁን እንጂ ዐቃቤ ሕግ ክሱን ሲያቀርብ የተምታታ ጉዳይ እንዳለ ዳኛው ተናግረዋል። በመሆኑም የነፃነት ታጋዩ በሕጋዊና ትክክለኛ ስማቸው አለመከሰሳቸውን ግልፅ ችሎቱ እንዲመለከት አቶ እስክንድር ነጋ ታዳሚውን ጠይቀዋል።

በተያያዘ ዜና መስከረም 12 ቀን 2013 ዓ.ም. በተካሄደው ችሎት ላይ ለመታደም የፍርድ ቤቱ ግቢ ውስጥ የእነ እስክንድር ነጋ ምስል የታተመበትን ካኔቴራ ለብሰው የተገኙ የፓርቲው አባላትና ደጋፊዎች ለ24 ሰዓታት በፖሊስ ታስረው ቆይተው እያንዳዳቸው በ2 ሺህ ብር ዋስ ተፈተዋል። ከእነዚህ መካከል የባልደራስ ጋዜጣ ከፍተኛ አዘጋጅ ወግደረስ ጤናው እና የአስቴር ስዩም ባለቤት መምህር በለጠ ጌትነት ይገኙበታል።

# በሆሳዕና የመስቀል በዓል እንዳይከበር ሀገረ ስብከቱ ከለከለ

በደቡብ ኢትዮጵያ ሆሳዕና ከተማ ውስጥ የመስቀል በዓል እንዳይከበር የአካባቢው ማለትም የሀድያና ስልጤ ሀገረ ስብከት ከልክሏል፡፡ ሀገረ ስብከቱ በዓሉ እንዳይከበር የከለከለው ቤተ ክርስቲያኗ ከ40 ዓመታት በላይ ስትገለገልበት የቆየችው የመስቀል ደመራ እና የጥምቀት በዓላት ማክበሪያ ቦታዋን በመንግሥት መነጠቋን በመቃወም ነው፡፡ በመሆኑም የዘንድሮው የደመራ በዓል በከተማዋ ፈፅሞ ሳይከበር ቀርቷል፡፡ አንዳንድ የከተማዋ ነዋሪዎች በየመንደራቸው ትንንሽ ደመራዎችን ቢደምሩም በዓሉን ያለማክበር አድማ በመጀመሩ በከፍተኛ የሀዘን ስሜት ውስጥ ሆነው ደመራውን ሳይለኩሱ አፍርሰው ችቦዎቹን ወደ ነበረበት መመለሳቸውን በስልክ ያነጋገርናቸው የቤተክርስቲያኗ አመራሮች ገልፀዋል፡፡ የሰንበት ተማሪዎችና ሌሎች የቤተክርስቲያኗ አገልጋዮች ዓይንና ጆሮዎቻቸውን በጥምጣም ሸፍነው በአንድ ላይ በአርምሞ በመቆም ተቃውሟቸውን ገልፀዋል፡፡ ከፊሎቹ ጥቁር ልብስ በመልበስ እና አንገታቸው በማቀርቀር በመንግሥት ላይ ያላቸውን ተቃውሞ የገለፁ ሲሆን የሃይማኖት አባቶችም አንገታቸውን ደፍተው በአርምሞ ታይተዋል፡፡ «የሆሳዕና ከተማ ገዳማትና 9ኙም አድባራት የጥምቀተ ባሕር ማክበሪያ ቦታ በሆሳዕና ከተማ አስተዳድር፣ በሀድያ ዞን አስተዳደርና በክልሉ መንግሥት በተደጋጋሚ በተወሰነው ውሳኔ መሠረት ይፈፀምልን!!!» የሚል የቢልቦርድ ማስታወቂያ በጋራ የያዙ አዳጊዎችም ዓይን እና ጆሮዎቻቸውን ሸፍነው በአርምሞ ታይተዋል፡፡

ቤተክርስቲያኗ ለዘመናት ስትጠቀምበት የባጀችው ቦታ ለገበያ ማዕከልነት ተሰጥቷል፡፡ ተለዋጭ ቦታ ከነካርታውና የይዞታ ማረጋገጫው በዚያው አቅራቢያ እንዲሰጣት የደቡብ ክልል የሕዝብ ተወካች ምክር ቤት ቢወስንም የከተማው አስተዳድር ተግባራዊ አላደረገውም፡፡ «ከተማው ባወጣው የመሬት አስተዳደርና መመሪያ መሠረት የይዞታ ማረጋጋጫ ለቤተክርስቲያኗ እንደማይሰጥ ተነግሮናል፡፡ አመታዊ በዓላትን በተመለከተ ቅድስት ቤተክርስቲያን ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋር በመጋራት ቦታውን እንድትጠቀምና ቦታውን የሚያስተዳድረውም መንግሥት እንደሆነ ተነግሮናል፡፡» ብለዋል ያነጋገርናቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የመረጃ ምንጮች፡፡ «እንኳንስ ከሌሎች ቤተ እምነቶች ጋር የአምልኮ ቦታ መጋራት ቤተክርስቲያን ለራሷ ምዕመናንም የምትፈቅዳቸውና የምትከለክላቸው የመቅድስ ክፍሎች አሉ፡፡ በጋራ ተጠቀሙ ማለት የቤተክርስቲያኗን ቀኖና የሚጋፋ ነው፡፡ መንግሥት ራሱ ያወጣው ሕግ እንኳን ግጭት እንዳይፈጠር የተለያዩ ሃይማኖቶች ቤተ እምነቶች በሚገነቡበት ጊዜ የተራራቁ እንዲሆኑ ይደነግጋል፡፡» ሲሉም ጨምረው ገልጸዋል ፡፡

# የደመራ በዓል በሞጆ፣ ናዝሬትና ደብረ ዘይት እንዳይከበር መንግሥት ከለከለ

የዘንድሮው የመስቀል ደመራ በዓል በተለያዩ የኦሮሚያ ‹ክልል› ከተሞች እንዳይከበር በመንግሥታዊ አካላት በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ ክልከላዎች እየተደረጉ መሆኑን በየአካባቢዎቹ ከሚኖሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ምዕመናን የደረሱን መረጃዎች አመላክተዋል፡፡ ሞጆ፣ ደብረ ዘይትና ናዝሬት የክልከላው ዋነኛ ሰለባዎች ሆነዋል፡፡ የምስራቅ ሸዋ ሀገር ስብከት ሊቀ ጳጳስ አቡነ ጎርጎሪዮስ ባለፈው መስከረም 9 ቀን 2013 ዓ.ም. በሞጆ ከተማ ተገኝተው የቤተክርስቲያኗ የአደባባይ በዓል የሆነው የመስቀል ደመራ በዓል የኮሮና ተህዋሲ ወረርሽኝን ባገናዘበ እንቅስቃሴ እንዲከበር ቢያዝዙም መንግሥት በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ገብቶ ከልክሏል፡፡ የከተማዋ ከንቲባ «የመስቀል በዓል እንዳይከበር ስለተከለከለ በከተማዋ ማክበር አይቻልም» ሲሉ ተደምጠዋል፡፡ የሀይማኖት አባቶች በዓሉ እንዲከበር ወደ ከንቲባዋ ቢሮ በተደጋጋሚ ቢመላለሱም በዓሉን በአደባባይ በድምቀት ማክበር ሳይቻል ቀርቷል፡፡

በተመሳሳይ የደብረዘይት ከተማ ከንቲባ አንዳች የበዓሉ አከባበር እንቅስቃሴ እንዳይደረግ አዝዘዋል፡፡ የአካባቢው የሃይማኖት አባቶች መንግሥት በዓሉ የሚከበርበትን ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርግ አስቀድመው ቢጠይቁም ከንቲባዋ ስለበዓሉ አከባበር ፈቃድ አለመስጠቱን እና ይህንኑ ከአለቆቻቸው አጣርተው እንደሚያሳውቁ ገልጸው እስከዚያው ግን እንቅስቃሴዎች እንዳይደረጉ አስጠንቅቀዋል፡፡ ከዚህ ስለቀጠለው ክስተት ለማጣራት ያደረግነው ሙከራ ለጊዜው አልተሳካም፡፡ ባለፈው ዓመት በተመሳሳይ ክልከላ በዓሉ በደብረዘይት ከተማ ሳይከበር መቅረቱ ይታወሳል፡፡

በተያያዘ ክልከላው በናዝሬት ከተማም ተፈፅሟል፡፡ ከአቡነ ጎርጎሪዮስ ጋር የተወያዩት የከተማዋ ከንቲባና የአካባቢው የገዥው ፓርቲ ተወካይ ከፀጥታ ስጋት ጋር በተያያዘ በዓሉ በአደባባይ እዲከበር ፈቃድ አለመስጠቱን ገልፀው ቁርጥ ያለ ክልከላም ሳይሰጡ የሃይማኖት አባቶችን እና ምዕመናኑን ሲያጉላሉ ቆይተዋል፡፡ በመጨረሻም በአደባባይ እንዳይከበር በመከልከሉ በየአጥቢያዎቹና በየመንደሩ በስጋት ውስጥ ሆኖ ተከብሯል፡፡ በተያያዘ ዜና በአዲስ አበባ ‹ክልል› መስቀል አደባባይ በደማቅ ስነ ስርዓት ይከበር የነበረው የመስቀል ደመራ በዓል ዘንድሮ አስቀድሞ በመንግሥት ፈቃድ በተሰጣቸው ጥቂት ሰዎች ብቻ ተከብሯል፡፡

## የባልደራስ - መኢአድ ምክር ቤት እስክንድር ነጋና ፕሬዚደንቱ አድርጎ መረጠ

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) እና የባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ (ባልደራስ) የጋራ ምክር ቤት መስከረም 9 ቀን 2013 ዓ.ም. ባካሄደው ጉባዔ ፕሬዚደንቱን እና ምክትል ፕሬዚደንቱን መርጧል፡፡ በዚህም መሠረት በእስር ላይ የሚገኙትን የነፃነት ታጋይ አቶ እስክንድር ነጋን ፕሬዚደንት አቶ ማሙሸት አማረን ደግሞ ምክትል ፕሬዚደንት አድርጎ መርጧል፡፡ ምክር ቤቱ መሪዎቹን የመረጠው በሙሉ የድጋፍ ድምፅ ነው፡፡ አቶ እስክንድር ከእስር እስከሚወጡም የፕሬዝደንቱን ሥራ ጨምረው ምክትሉ ያከናውናሉ፡፡ 20 አባላት ያሉት የቅንጅቱ ምክር ቤት የኮሮና ተህዋሲ ባስከተለው ከ4 ሰዎች በላይ ያለመሰብሰብ ገደብ ምክንያት ስብሰባዎችን ማድረግ ባለመቻሉ መሪዎቹን ሳይመርጥ ቆይቷል፡፡

አቶ እስክንድር ነጋ ከ1984 ዓ.ም. ጀምሮ በጋዜጠኝነት ሙያቸው የሕወሓት/ኢሕአዴግን መንግሥት አምባገነናዊ ገመናዎችን ሲያጋልጡ ቆይተዋል፡፡ በዚህም ኢትዮጲስ፣ ሳተናው፣ ምኒልክና አስኳል የተባሉ የአማርኛ ጋዜጦችን ከባለቤታቸው ጋዜጠኛ ሰርካለም ፋሲል ጋር በመሆን በባለቤትነት ሲያሳትሙ ቆይተዋል፡፡ በዚሁ ሥራዎች በአገዛዙ ከነባለቤታቸው በተደጋጋሚ ለእስራትና እንግልት ተዳርገዋል፡፡ ወንድ ልጃቸው ናፍቆት እስክንድርንም ባለቤታቸው የተገላገሉት በእስር ቤት ውስጥ ነበር፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት የአማርኛ ጋዜጦች በተጨማሪ ሐበሻ የተባለ ሳምንታዊ የእንግሊዝኛ ጋዜጣም ሲያሳትሙ የነበሩ ሲሆን ሁሉም ጋዜጦች በአገዛዙ በኃይል ተዘግተዋል፡፡ አቶ እስክንድር ካለፈው ዓመት ጀምሮ ደግሞ ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲን በማቋቋም በፕሬዚደንትነት እየመሩት ይገኛሉ፡፡

አቶ ማሙሸት አማረ በፓርቲ ፖለቲካ ውስጥ ከ1984ቱ የመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅት (መዐሕድ) ምሥረታ ጀምሮ ልምድ አላቸው፡፡ ለፍትሕ እና ለዴሞክሲ በሚያደርጉት የነፃነት ትግልም በተደጋጋሚ ለእስራትና እንግልት ተዳርገዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የመኢአድ ፕሬዚደንት በመሆን እየታገሉ ይገኛሉ፡፡

# አሸባሪው መንግሥት ወይስ እስክንድር?





### መንደርደሪያ

‹‹. . . ሕዝብን የምትጨቁኑበትን መንግሥት በፍፁም እቃወማለሁ:: በዚህ ምክንያት ልትገድሉኝ ትችላላችሁ:: ሞት ስትፈርዱብኝም የምፀፀት ይመስላችኋል:: እኔ በዚህ ብፀፀት እንደናንተ ቂል ነኝ:: መጥፎ ሥራችሁን እና ሕዝብን መጨቆናችሁን የምትተው ካልሆነ መቶ ጊዜ እሞታለሁ:: እንደገና ብወለድ መቶ ጊዜ የገደላችሁኝ መሆናችሁንም ባስታውስ ይህ መቀጣጫ ሁኖኝ ዝም ልላችሁ አልችልም::. . .›› ይህ ንግግር የሀቀኛው እና የእምቢተኛው ደራሲ የአቤ ጉበኛ  ነው:: አቤ ይህንን ሃሳብ ‹አልወለድም› በተሰኘው ድርሰቱ ጽፎት ብቻ አላለፈም፤ የሕይወቱ መመሪያ አድርጎት በመንግሥት ስለት አልባ መሳሪያ ማለትም በዱላ ተደብድቦ እስከተገደለበት ጊዜ ድረስ ኑሮበታል እንጂ:: ከዚህ ተንደርድረን በቀጥታ ወደ ሰሞነኛው የእነ እስክንድር ነጋ የሽብር ክስ እንለፍ::

### የሽብር ክስ ከአሸባሪው መንግሥት

መጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም. ጠቅላይ ሚንስትር አብይ አሕመድ ከኢሕአዴግ ምክር ቤት ውስጥ ተመርጠው የጠቅላይ  ሚንስትርነትን ሥልጣን ሲረከቡ ብዙዎችን ያስደሰቱት ያለፈ ጥፋታቸውን በመናዘዛቸው ነበር:: ከኑዛዜያቸው ዋነኛው ሊባል የሚችለው ደግሞ ‹‹አሸባሪዎች እኛ ነን›› ማለታቸው ነበር:: በዚህ ንግግራቸው ችኩል ምሁራንም ጭምር ‹‹ከሰማይ የወረዱ የእግዚአብሔር መልዕክተኛ፣ በፈርኦን ቤት ያደገ ሙሴ›› ሲሉ አወድሰዋቸዋል:: ሆኖም እንኳን ከመለኮታዊው ሰማይ ከትንሽ ዛፍ እንኳን አለመውረዳቸውን ድርጊቶቻቸው ዕለት በዕለት እያሳበቁባቸው መጡ:: ▶

እነሆ ዛሬ የወረወሩትን የፀረ ሽብር አዋጅ ከጣሉበት አቧራውን አራግፈው በማንሳት እስክንድር ነጋን እና የትግል አጋሮቹን ዳግም ከሰውበታል። በዚህ አዋጅ የባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ (ባልደራስ) ፕሬዚደንት አቶ እስክንድር ነጋ፣ የድርጅት ጉዳይ ሓላፊው አቶ ስንታየሁ ቸኮል፣ ወ/ሮ አስቴር ስዩም እና አስካለ ደምሌን ጨምሮ ሰባት የፓርቲው አመራሮችና አባላት ተከሰዋል። አቶ እስክንድር ነጋ የመንግሥትን አምባገነናዊነት በጋዜጠኝነት ሙያቸው ዘርዝረው በማጋለጣቸው በሕወሓት/ ኢሕአዴግ በተመሳሳይ የሽብር ክስ ታስረው እንደነበር አይዘነጋም። የ18 ዓመታት እስር ተፈርዶባቸው 7 ዓመታት ለሚጠጋ ጊዜ አሁን በሚገኙበት ቃሊቲ እስር ቤት ታስረው ቆይተዋል። በኋላም ሕወሓት ፖለቲካዊ አቅሙ እየተሸመደመደ ሲመጣ በይቅርታ ከተለቀቁ 746 እስረኞች መካከል አንዱ ሆነው ተፈቱ። በወቅቱ የቀረበባቸው የሽብር ክስ «ከኤርትራ የጦር መሳሪያ በመቀበል፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የሽብር ወንጀል ፈፅመዋል» የሚል ነበር። ይህ የክስ ሰነድ በችሎት ላይ ሲነበብ እንኳንስ በሕዝብ ዘንድ በራሳቸው በዳኞቹና በዐቃቢያነ ሕጎች ዘንድም ቢሆን ከቴአትር ‹ስክሪፕትነት› የዘለለ ትርጓሜ አልተሰጠውም።

‹አሸባሪዎች እኛ ነን› ያሉት የዛሬው ጠቅላይ ሚንስትር ግን እውነትም የወቅቱ አሸባሪ እሳቸው ነበሩ። ምክንያቱም ባለፈው ዓመት በሐረር እና በአንቦ በነበራቸው ተከታታይ ሕዝባዊ ውይይቶች እንደነገሩን፤ እንዲሁም የኦነግ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባሉ አቶ ለሚ ቤኛ በአንድ ቃለ መጠይቃቸው እንዳረጋገጡት አብይ አሕመድ በኦሕዴድ የፓርቲና የመንግሥት መዋቅር ውስጥ ቢሆኑም የኦነግ ሰላይ ነበሩ። በወቅቱ ኦነግ የትጥቅ ትግሉን ኤርትራ ውስጥ መሽጎ ያካሂድ ነበር። አብይ አሕመድ ደግሞ በብሔራዊ የመረጃና ደህንነት መሥሪያ ቤት ውስጥ ያገለግሉ ነበር። በዚህም ለወቅቱ አሸባሪ ተቋም ኦነግ ሚስጥራዊ መረጃዎችን ያደርሱት እንደነበር ራሳቸው በአንደበታቸው ተናግረዋል። በተመሳሳይ በዚያው በኤርትራ ሌላኛው በአሸባሪነት መዝገብ ሰፍሮ ለነበረው ለአርበኞች ግንቦት 7 ይሰልሉ እንደነበርም መረጃዎች ይፋ ሆነዋል። በመሆኑም የሁለቱም ድርጅቶች መደበቂያ ከነበረችው ኤርትራ ጋር ወታደራዊም ሆነ የሲቪል ግንኙነት የነበራቸው እኚሁ የዛሬው ጠቅላይ ሚንስትር ናቸው ማለት ነው። በመሆኑም ከኤርትራ የጦር መሳሪያ ተቀብለው የሽብር ወንጀል የፈጠረው እስክንድር ነጋ ሳይሆን አብይ አሕመድ ናቸው ብሎ መደምደም ይቻላል። ጠቅላይ ሚንስትሩ ሥልጣን ላይ እንደወጡ በአጭር ጊዜ ውስጥ የኢትዮ ኤርትራን ግንኙነት ወደ ሰላማዊ መንገድ ያመጡት ከዚህ ከዚህ በቀጠለው ከአለቆቻቸው አለቃ ማለትም ከኢሳያስ አፈወርቂ ጋር በነበራቸው ግንኙነት እንደሆነ መገመት ስህተኛ አያስብልም።

ጠቅላይ ሚንስትሩ ሥልጣን ከያዙ ጀምሮ ባሉት ዓመታት ውስጥ በኢትዮጵያ እጅግ ዘግናኝ የግድያ ዓይነቶች ተፈፅመዋል። በኦሮሚያ እና በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልሎች ውስጥ በሚኖሩ ሰዎች በአማራነታቸውና በኦርቶዶክስነታቸው መንግሥታዊ የዘር ፍጅት ተፈጽሞባቸዋል። ዜጎች በቢላዋ ታርደው ስጋቸው ተቆራርጦ ተጥሏል። አንገቶቻቸው በገጀራ ተቀንጥሰዋል። አስከሬኖች በእሳት ተቃጥለዋል። ካህናት ከነነፍሳቸው ጉድጓድ ውስጥ ተቀብረው ተገድለዋል። ነፍሰ ጡር ሴት ሆዷን በሳንጃ ተሰንጥቃለች። የሰው አስከሬን መንደር ለመንደር በሞተር ሳይክል ተጎትቷል። ሌላውም በአደባባይ ተዘቅዝቆ ተሰቅሏል። እነዚህና ሌሎችም በርካታ ግፎች ተፈጽመዋል። እነዚህን አሰቃቂ ወንጀሎች ነፍሰ ገዳዮቹ የፈጸሙት በኦሮሚያ ፖሊስ እና በልዩ ኃይል ድጋፍ መሆኑን ራሱ ገዥው ፓርቲም የሚያምነው ሀቅ ነው። ይህ ሁሉ ሲፈጸም ህግ ማስከበር ይገባቸው የነበሩት የሀገር መከላከያ ሠራዊት፣ የፌዴራል ፖሊስ እና የአካባቢው ባለሥልጣናት ቆመው ተመልካች መሆናቸው ጉዳዩን የበለጠ እንቆቅልሽ ያደርገዋል። ታዲያ ይህ ሽብርተኝነት አይደለምን? ከዚህ በመነሳት መከላከያ ሠራዊቱን በበላይነት የሚያዙት ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አሕመድና መንግሥታቸው አሸባሪዎች አይደሉም ማለት ይቻላልን? እነ ስንታየሁ ቸኮል የተከሰሱት ይህንን የሽብር ድርጊት በማጋለጣቸው እንደሆነ ለፍድር ቤቱም በችሎት ላይ ተናግረዋል።

## ዶሴው

የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በእነ እስክንድር ነጋ ላይ ያቀረበው ክስ በአጭሩ «ማናቸውንም አጋጣሚዎች ብሔርን እና ሀይማኖትን መሰረት ያደረገ ግጭት መቀስቀሻ እና ማነሳሻ መሣሪያ አድርገው በመጠቀም መንግሥትን ሰላም ነስተዋል። መንግሥት እንዳይረጋጋ አድርገው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳድር ሥልጣንን በኃይል ለመያዝ ሞክረዋል። አድማ አድርገዋል። የሀጫሉ ሁንዴሳን ሞት እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም በኦሮሞና ትግሬ ብሔሮች ላይ እንዲሁም በሙስሊሞች ላይ ጥቃት እንዲፈፀም አዘዋል። ለዚህም ወጣቶችን አደራጅተዋል። መርተዋል። በመሆኑም ሰኔ 23 እና ሰኔ 24 ቀን 2012 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ አካባቢዎች በተፈጠረ የእርስ በእርስ ግጭት የ14 ሰዎች ሕይወት እንዲያልፍ በማድረጋቸው በቀጥታ በወንጀሉ ተጠያቂ ናቸው። በፓርቲያቸው ውስጥ ኦሮሞዎችና ትግሬዎች እንዳይገቡ አድርገዋል። በተቻለ መጠን ሙስሊሞችም ወደ ፓርቲው እንዳይመጡ፤ ከመጡም ከፍተኛ ሚና እንዳይኖራቸው አድርገዋል። ታከለ ኡማን ለመግደል ከአዲስ አበባና ከአማራ ‹ክልል› መልምለው ወታደር አሰልጥነዋል።» የሚል ነው።

‹መንግሥትን በተለይም የቀድሞውን የአዲስ አበባ ምክትል ከንቲባ ታከለ ኡማን ሰላም መንሳት› የሚል ክስም ቀርቦባቸዋል። ‹ሕገ ወጥ መታወቂያ የሚያድለውን፣ የዜጎችን መኖሪያ ቤቶች በማንነታቸው እየለየ የሚያፈርሰውን እና የሚያፈናቅለውን ታከለ ኡማን ማስጨነቅ ሥራችን ነው።› ሲሉ ነበር አቶ ስንታየሁ ቸኮል ሐሙስ መስከረም 7 ቀን 2013 ዓ.ም. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት በተካሄደው ችሎት ለፍርድ ቤቱ የተናገሩት። በዚሁ ችሎት የባልደራስ ሊቀመንበር አቶ እስክንድር ነጋ «ገዥው ፓርቲ በፖለቲካ ውሳኔ ምክንያት ወደ እስር ቤት ያወረደን መሆኑን ልታውቁት ይገባል።» በማለት ዳኞችን አሳሰበዋል። ከእስር ተለቀው መጭውን ምርጫ መሳተፍ እንዳለባቸውም ጠቁመዋል። ሕወሓት/ ኢሕአዴግ ማዕከላዊ መንግሥቱን ተቆጣጥሮ በነበረበት ጊዜም በፖለቲካ ተሳትፏቸው ምክንያት በተደጋጋሚ ለእስር የተዳረጉት ወይዘሮ አስቴር ስዩም በበኩላቸው «ፖለቲከኛ ነኝ። የሕግ አንቀፅ ጠቅሼ ላልከራከር እችላለሁ። የፖለቲካ ሕግ ጠቅሼ ባስረዳ ግን ክሱ ፖለቲካዊ በቀል ነው። ዳኞች ወደ ህሊና ፍርዳችሁ ተመለሱ። ስርዓት ያልፋል። ሕዝብ አያልፍም። ታሪክ አያልፍም። ስለዚህ ይህንን አስባችሁ ለህሊናችሁ ፍረዱ።» ብለዋል።

በመቀጠል አስካለ ደምሌ «ድርጊቱ ተፈፀመ በተባለበት ጊዜ የመንግሥት ሠራተኛ ስለሆንኩ ወደ መንግሥት መሥሪያ ቤት ቢሮዬ ሄጄ ነበር። የባልደራስ ቢሮ ውስጥ ነበርሽ የተባልኩት ስህተት ነው። የፓርቲው አባልና አመራር ብሆንም በተጠቀሰው ጊዜ እዚያ አልነበርኩም። የፖለቲካ ተሳትፎዬን ልነፈግ አይገባም። የሃይማኖትም ሆነ የብሔር ጥላቻም የለኝም።» ብለዋል። ችሎቱ እነ እስክንድር ነጋ የዋስትና ጥያቄያቸውን ያቀረቡበትም ነበር።

## የተከሳሽ ጠበቃዎች በዚሁ ችሎት

«አንድ ተከሳሽ የዋስትና መብቱን የሚነጠቀው አደገኛ ጉዳት አድራሽ ከሆነ ነው። ደንበኞቻችን የፖለቲካ ፓርቲ እየመሩ የሃሳብ ትግል እያደረጉ ያሉና ቋሚ አድራሻ ያላቸው በመሆናቸው የዋስትና መብታቸው ሊከበር ይገባል። በደረቅ ወንጀል ተጠርጥረው አያውቁም። ብጥብጥ አስነስተዋል የተባለው ሀሰት ነው። እንዲያውም ሀገር የምትበጣበጠው እነርሱ ያለ ወንጀላቸው በመታሠራቸው ነው። ክሱ «ብሔርን ከብሔር ለማጋጨት ሞክረዋል። ሃይማኖትን ከሃይማኖት ለማጋጨት ሞክረዋል» የሚል ነው። ነገር ግን «እንኳንስ ግጭት ሳይፈጥሩ ይቅርና ዐቃቤ ሕግ ያለው ነገር ተፈፅሞ እንኳን ቢሆን የብሔርም ሆነ የሃይማት ግጭት ማስነሳት የዋስትና መብት ይከለከላል የሚል አንቀፅ የለም። ዐቃቤ ሕግ ያቀረበው ክስ የተብራራ አይደለም። ማን፣ መቼ፣ የት፣ ምን ወንጀል ፈፀመ? የሚለው ▶

ተብራርቶ መቅረብ ነበረበት::» ብለዋል:: በዚህ ችሎት የክስ ሰነዱ ተነቦ በዐቃቤ ሕግ ተጨማሪ የቃል ማብራሪያ ከተሰጠበት በኋላ ነው ጠበቃዎችና የነፃነት ታጋዮች ሀሳባቸውን የሰነዘሩት:: ዳኞች አቤቱታዎችን ከመስማት በዘለለ የሰጡት ብይን የለም:: ለሌላ ጊዜ ቀጠሮ ሰጥተው ችሎቱ ተበተነ::

### ማክሰኞ፤ መስረም 12 ቀን 2013 ዓ.ም.

እነኝህ ሁለቱ ችሎቶች በጥቂቱም ቢሆን ሕዝብ የሚታደምባቸው ግልፅ ችሎቶች ናቸው:: ከላይ በተጠቀሰው ችሎት በአንፃራዊነት በርከት ያሉ ዜጎች ያልታደሙ ሲሆን በዚህኛው ችሎት ግን ግልፅ ችሎት መሆኑ በመታወቁ እና በርካታ ሰው በመምጣቱ ጥቂት የቤተሰብ እና የፓርቲው የአመራር አባላት ብቻ ናቸው እንዲገቡ የተፈቀደላቸው::በዕለቱ የእስክንድር ነጋ፣ የስንታየሁ ቸኮል፣ የአስቴር ስዩም እና የአስካለ ደምሌ ምስሎች የታተሙባቸው ካኒቴራዎችን ለብሰው በፍርድ ቤቱ ግቢ ውስጥ የተገኙ አባላትና ደጋፊዎች በፖሊስ ተወስደው ታስረዋል:: ከእነኝህ መካከልም የባልደራስ ጋዜጣ ከፍተኛ አዘጋጅ ወግደረስ ጤናው እና የአስቴር ስዩም ባለቤት መምህር በለጠ ጌትነት ይገኙበታል:: እስክንድር ነጋ ዳኛውን ተከታታይ መስቀለኛ ጥያቄዎች የጠየቁበት፣ ዳኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክር መስለው የቀረቡበት መሆኑን ይህኛውን ችሎት ካለፈው ልዩ ያደርገዋል::

### ዳኞች በዚህ ችሎት

‹‹ክሱ ብሔርን እና ሀይማኖትን መሰረት በማድረግ ብጥብጥ መፍጠርን የሚመለከት ነው:: ነገር ግን የዐቃቤ ሕግ ክስ እያንዳንዱን ወንጀል በዝርዝር አይገልፅም:: ሰኔ 23 እና ሰኔ 24 ቀን 2012 ዓ.ም. ምን ያህል እና ምን አይነት ጉዳት እንደደረሰ አይገልፅም:: ጠበቆች ያቀረቡት የዋስትና ጥያቄ ነው:: ይህ ደግሞ ሕገ መንግሥታዊ መብት ነው:: ስለዚህ ይህንን በትክክል ገምግመን መወሰን እንድንችል ዐቃቤ ሕግ እንደገና አሻሽሎ ያቅርብ:: የደረሰው ጉዳት ከነሰዓቱና ትክክለኛ ቦታው መጠቀስ አለበት:: የትኞቹ ተከሳሾች እንደፈፀሙት ተለይቶ መቅረብ አለበት:: በአዲስ አበባ የትኞቹ ቦታዎች እንደተፈፀመም በትክክል ይገለፅ::›› ብለዋል ዳኞች:: በዚህ መሰረት ተሻሽሎ ለመስከረ 19 ቀን 2013 ዓ.ም. እንዲቀርብም ፍርድ ቤቱ አዝዟል:: ከዚህ በመቀጠል የነፃነት ታጋዮቹ በቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ ያሉበትን ሁኔታ በተመለከተ አቤቱታዎችን አሰምተዋል::

አስቴር ስዩም

‹‹ከቀናት በፊት አዲስ አበባ ፖሊስ ጣቢያ በነበርኩበት ጊዜ ቤተሰቤ ልጄን እያመጣልኝ ጡት አጠባ ነበር:: ቃሊቲ ከሄድኩ በኋላ ማጥባት ተከልክያለሁ:: ልጄ እያለቀሰች ነው:: ጨቅላዋን ሳጠባ ታላቁ ልጄም በናፍቆት እየተጎዳ ስለሆነ አይቶኝ እንዲሄድ እንዲፈቀድልኝ እጠይቃለሁ:: ያመኛል:: ‹የስፓይናል ኮርድ› ችግር አለብኝ:: ስለዚህ ስለማጠባም ጭምር ምግብ ቤተሰቤ እንዲያመላልስልኝ እንዲፈቀድልኝ እጠይቃለሁ::›› ብለዋል:: ወይዘሮ አስቴር ስዩም ይህንን ሲሉ ባለቤታቸው አቶ በለጠ ጌትነት ወደ ችሎት አዳራሹ ሊገቡ ሲሉ በፖሊስ ተይዘው ወደ 5ኛ ፖሊስ ጣቢያ ተወስደዋል::

### እስክንድር ነጋ እና ዳኛው በግልፅ ችሎት

**እስክንድር፡-** በቅድሚያ ቤተሰባዊ ጉዳዮችን ላንሳ:: ባለቤቴን እና ልጄን (ከአሜሪካ) በስልክ እንዳገኛቸው ይፈቀድልኝ:: ምስክር አሰማሙን በተመለከተ. . .

**ዳኛው፡-** ይቆዩ:: እሱን አሁን አናዳምጥም::

**እስክንድር፡-** ዐቃቤ ሕግ ክሱን እንዲያሻሽል ትዕዛዝ ተሰጥቷል::

**ዳኛው፡-** ይቆዩ አቶ እስክንድር

**እስክንድር፡-** ሁለተኛው ክስ እንዲሻሻል አላመናችሁበትም ማለት ነው? እንዲሻሻሉ ከተዘረዘሩት ውስጥ አልተጠቀሰም::

**ዳኛው፡-** እሱን ለመወሰን ቀሪ ሥራዎች አሉን:: አልገመገምነውም::

**እስክንድር፡-** 7ኛ ተከሳሽን በተመለከተ ባለፈው ችሎት ያቀረብነው አቤቱታ አለ:: ዐቃቤ ሕግ ፤የተለያዩ ስሞችን ተጠቅሟል፣ ነው የሚለው:: አቤቱታችን አሁን የተከሰስነው በሕጋዊ ስሙ አይደለም የሚል ነው:: ዐቃቤ ሕግ ‹ከእስር ቤት ያመለጠ› ነው የሚል ውንጀላም አቅርቧል:: ከእስር ቤት ሲያመልጥ በዚህ ስም ይታወቅ ነበር ወይ? ይሄን ጥያቄ ብትመልሱልን ወደ ፍሬ ሃሳቡ፤ ወደ ዝርዝሩ መግባት እንችላለን::

**ዳኛው፡-** ዐቃቤ ሕግ ሲያቀርብ ብዥታ አለ:: (ከጎናቸው ካሉ ሌሎች ሁለቱ ጋር በሹክሹክታ ከተመካከሩ በኋላ የተሰጠ ምላሽ ነው:: ዐቃቤ ሕጉ ከዳኛው ፊት ለፊት በዝምታ ቆመዋል)

**እስክንድር፡-** ስለዚህ ሕጋዊ ስሙ አይደለም ማለት ነው:: ግልፅ ችሎቱ እንዲያውቅልኝ እፈልጋለሁ:: (አቶ እስክንድር ፊታቸውን ወደ ታዳሚው በማዞር በአፅንኦት አሳሰቡ)

**ዳኛው፡-** አይ፤ ከጠበቆቻችሁ ጋር ምከሩና የክስ መቃወሚያ አቅርቡ::

**እስክንድር፡-** ከእስር ቤት ሲያመልጥ በዚህ ስም ይታወቅ ነበር ወይ? ዐቃቤ ሕጉ እዚህ ቁመዋል:: ይሄ በቀላሉ መመለስ የሚችሉት ጥያቄ ነው::

**ዳኛው፡-** ጠበቆች ሌላ ጥያቄ አላችሁ? አጠገባቸው ካሉት ሌሎች ሁለቱ ጠበቆች ጋር የተወሰነ ጊዜ በሹክሹክታ ሲመካከሩ ከቆዩ በኋላ) ከአራቱ

**ጠበቆች አንዱ፡-**ደንበኞቻችን ከክሱ ስዕል ውጭ ናቸው:: ጉዳዩ ከእነርሱ ጋር ግንኙነት የለውም:: ይህንን መቃወሚያ እንድናቀርብ ቀጠሮ ይያዝልን::

**እስክንድር፡-** ዐቃቤ ሕጉ ቁመዋል:: የ7ኛ ተከሳሹን ስም ጉዳይ ይመልሱልን:: ለምንድን ነው ለሌላ ቀን የምናዘዋውረው:: ተከሳሹ ከእስር ቤት ሲያመልጥ በዚህ ስም ይታወቅ ነበር ወይ?

(ዳኛውና ዐቃቤ ሕጉ ፀጥ አሉ:: በመሀል እጃቸውን ሲያወጡ ለነበሩት ለአቶ ስንታየሁ ቸኮል ዕድል ተሰጠ::)

**ስንታየሁ፡-** በሕግ ጥበቃ ስር ያለን ሰዎች አገልግሎት የማግኘት መብት አለን:: አገልግሎቶቹ ተቋርጠዋል:: አሁን እንደተመለስን አገልግሎቶች እንዲሰጡን ትዕዛዝ ይስጡልን:: ቤተክርስቲያን እንዳይቃጠል ከልክላችኋል ተብለን ነው የተከሰስነው:: መፀለይ አልቻልንም:: ቤተክርስቲያን እስር ቤት ግቢ ውስጥ እንዲሠራልን እጠይቃለሁ:: ከባለቤቴ እና ከልጆቼ ጋር መገናኘት እፈልጋለሁ:: ቤተሰብ እንዲጠይቀን ይፈቀድ::

(አቶ እስክንድር የስንታየሁን ትንፋሽ ተከትለው ቀጠሉ)

**እስክንድር፡-** እባክዎን ዐቃቤ ሕጉ ምላሽ እንዲሰጡ ያድርጉልኝ::

**ዳኛው፡-** ከባለቤትዎ እና ከልጅዎ ጋር በስልክ እንዲገናኙ ትዕዛዝ ተሰጥቷል:: (ጥያቄውን አለፉት)

**አስካለ፡-** ዐቃቤ ሕግ የከሰሰኝ በወቅታዊ ጉዳይ በሚል ነው:: ‹‹ፎቶሽን ከእስክንድር ጋር አይተናል:: ባልደራስን ትደግፊያለሽ›› በሚል ነው የተከሰስኩት:: የመንግሥት ሠራተኛ በመሆኔ የራሴ የፖለቲካ አስተሳሰብ እንዳይኖረኝ ገደብ እየተደረገብኝ ነው:: ‹‹የመንግሥት ደሞዝ እየተከፈላቸው ባልደራስን የሚደግፉ›› በሚል ክስ ነው እስር ቤት የወደቅኩት:: በፖለቲካ አስተሳሰቤ የመደራጀት መብቴ ይከበር:: ቤተሰቦቼ ክፍለ ሀገር ናቸው:: በስልክ እንዳገኛቸው ይፈቀድልኝ::

ዳኛው፡- የምታነሱት ጥያቄ በቀላሉ መዝግበነው የምንሄደው አይደለም:: የህክምና እና መሰል አፋጣኝ ጉዳዮችን ትዕዛዝ እንሰጥባቸዋለን:: ሌሎች አፋጣኝ ያልሆኑ ጉዳዮችን በሂደት እንነጋገርባቸዋለን::

በአጠቃላይ የባልደራስ አመራሮች የተከሰሱበት የፀረ ሽብር አዋጁ ከሕገ መንግሥት ተብየው ጋርም የሚጣረስ ነው:: አሮጌው ኢሕአዴግም ሆነ አዲሱ የአብይ አሕመድ ኢሕአዴግ በሰላማዊ ትግል ለሥልጣናቸው የሚያሰጓቸውን ፖለቲከኞች ለማፈን የሚጠቀሙበት መሳሪያ ነው:: ጋዜጠኞች ገመናቸውን እንዳያወጡ የሚቆርቡበትም ነው:: በሕገ መንግሥት ተብየው አንቀፅ 20 መሰረት አንድ ተከሳሽ ምስክሮችን የማወቅና የመጠየቅ መብት አለው:: የፀረ ሽብር አዋጁ አንቀፅ 32 (1) ምስክሮች ስማቸውና አድራሻቸው እንዳይገለፅ ይደነግጋል:: ይህም ክልከላ በፍርድ ቤቱ መዝገብ ላይም ይሁን በሚሰጣቸው ትዕዛዞች ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ እንዳይገለፅ እስከማድረግ የሚደርስ ነው:: የመጋረጃ ጀርባ ምስክሮችም የሀገሪቱ የበላይ ሕግ ተብየውን በመጣስ በዚህ መልኩ የመጡ ናቸው::



# አማራንና ኦርቶዶክስን እንደ አውሬ ...

በኢትዮጵያ የዱር እንስሳትን መግደል ወንጀል ነው:: ያስቀጣል:: ለእንስሳቱ ጥብቅና የሚቆም መንግሥታዊ ተቋምም አለ:: ሌላው ቀርቶ ይህ ተቋም ‹አውሬ› በሚል ስያሜ እንኳን እንዲጠሩበት አይፈቅድም:: ስለዚህም ‹የዱር አራዊት ይባል የነበረውን አጠራር› ‹የዱር እንስሳት› በሚል እንዲጠሩ አድርጓል። ካለፉት 30 ዓመታት ጀምሮ አማራ ላይ እየተፈፀመ ያለው ግፍ ግን ፍጡራን ላይ ከደረሰው ሁሉ እጅግ የመረረ መንግሥታዊ አረመኔያዊነት ነው:: ሕወሓት/ኢሕአዴግ ሥልጣን ላይ በወጣ ማግሥት ከኦነግ ጋር በደቦ የቻለውን ያህል አማራን እያሳደደ ገድሏል:: በተለይም በሽግግር መንግሥቱ ወቅት ኦነግ በአርባ ጉጉ፣ በበደኖ እና በወተር እጅግ አሰቃቂ ተግባራትን ፈፅሟል:: እረኛ ሕፃናትን ከሜዳ አግቶ ከወሰደ በኋላ ከነነፍሳቸው ቆዳቸውን ገፎ፤ ከሞቱ በኋላም ቆዳቸውን የጀግንነቱ መገለጫ አድርጎ በክብር ያስቀምጥ እንደነበር መዛግብት አስፍረውታል::

ይህ ታሪክ ሆኖ አላበቃም:: ዛሬም ተጠናክሮ ቀጥሏል:: በአማራ ሕዝብ ላይ የደረሰው ግፍ እውቁን የቀዶ ሕክምና ሊቅ ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስን ወደ ፖለቲካው መድረክ ስቧቸዋል:: ከእሳቸው የቀጠለው እንቅስቃሴ ዛሬ የአማራ ብሔርተኝነት ተጠናክሮ እንዲወጣ አድርጓል:: ሆኖም በተለያዩ አካባቢዎች አሁንም የአማራው ግድያ፣ ዝርፊያ እና ማሳደድ ሳያባራ ቀጥሏል:: በኦሮሚያ እና በቤንሻንጉል ባለፈው አንድ ዓመት ብቻ በአማራው ሕዝብ ላይ ተደጋጋሚ ጅምላ ጭፍጨፋዎች ተፈፅመዋል:: እነኝህ አማራን የማፅዳት እንቅስቃሴዎች በመንግሥት የታገዙ እንደሆኑም ዘገባዎች ያመላክታሉ:: ይህ ጅምላ ጭፍጨፋ በኦሮሚያ ነፍጠኛ በሚል መለያ የተፈፀመ ሲሆን በቤንሻንጉል ጉምዝ ደግሞ ‹ቀይ› በሚል ታርጋ የተፈፀመ ነው:: በሁለቱም አካባቢዎች እየተፈፀሙ ያሉ ጥቃቶች አማራን እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አማኞችን ማጥፋት ላይ ያለሙ ናቸው:: በድርጊቱ ገዥው ፓርቲና መንግሥት፣ ኦነግ፣ ሕወሓትና የውጭ ሀገራት የጋራ ጠላት ያሉትን አማላራን ለማጥቃት ተሳታፊዎች መሆናቸውን እየተፈፀሙ ካሉት የተለያዩ ተግባራት መረዳት ይቻላል።

በጳጉሜን 1 ቀን 2012 ዓ.ም. እንዲሁም ከመስከረም 4 እስከ መስከረም 10 ቀን 2013 ዓ.ም. ቢያንስ በሁለት ዙር በቀድሞው ጎጃም ክፍለ አገር በዛሬው ቤንሻንጉል ጉምዝ ‹ክልል› መተከል በአማራ/አገው ላይ ጅምላ ጭፍጨፋዎች ተፈፅመዋል::

በመተከል ዞን፣ ቡለን ወረዳ ኤጳር ቀበሌ በጅምላ ጭፍጨፋው የተገደሉ ዜጎች ስም ዝርዝር፡-

1. ይበሉ ጌታሁን:- ዕድሜ 35 ዓመት
2. ጥላሁን አበበ:- ዕድሜ 16 ዓመት
3. መኩሪያው አበበ፡- ዕድሜ 20
4. በቀለ አየነ ፡- ዕድሜ 35
5. አለሚቱ በሪሁን፡- ዕድሜ 25
6. ህይወት በቀለ፡- ዕድሜ 7
7. ካሰች በቀለ፡- ዕድሜ 17
8. ንጉሴ በሪሁን፡- ዕድሜ 35
9. ሀብታሙ፡- ዕድሜ 30 (የአባት ስም ለጊዜው ያልታወቀ)
10. አደራው፡- ዕድሜ 25 (የአባት ስም ለጊዜው ያልታወቀ)
11. አገኘሁ ጌታሁን፡- ዕድሜ 30
12. ደረጀ አገኘሁ፡- ዕድሜ 10
13. የወርቃየሁ ተፈራ፡- ዕድሜ 35
14. ይታይሽ ምህረት፡- ዕድሜ 30



15. ዮህንስ ወርቃዬሁ፡- ዕድሜ 7
16. ግዛቸው ወርቃየሁ፡- ዕድሜ 3
17. ቻላቸው ወርቃየሁ፡- ዕድሜ 3
18. ዘመን ወርቃየሁ፡- ዕድሜ 6
19. የሰራሽ ገሰሰ፡- ዕድሜ 35
20. በልስቲ ስጦታው፡- ዕድሜ 17
21. እየሩስ ስጦታው፡- ዕድሜ 15
22. አየነው ስጦታው፡- ዕድሜ 13
23. ንጉሴ ስጦታው፡- ዕድሜ 25
24. ባቢ ላቀ ዕድሜ፡- ዕድሜ 20
25. ካሳሁን አማረ፡- ዕድሜ 19
26. ቢሻው በላይ፡- ዕድሜ 40
27. ብርቱካን አሰፋ፡- ዕድሜ 30
28. ታየ ቢሻው፡- ዕድሜ 15
29. ጊወርጊስ ቢሻው፡- ዕድሜ 13
30. ባንቿአምላክ ቢሻው፡- ዕድሜ 7
31. ሚጣ ቢሻው፡- ዕድሜ 3
32. መኮንን ሽታሁን፡- ዕድሜ 30
33. ፈንታነሽ ፈቃዱ፡- ዕድሜ 25
34. ጉዳይ አለማየሁ፡- ዕድሜ 22
35. ትግስት መኮንን፡- ዕድሜ 4
36. ሀብተማርያም መኮንን ፡- ዕድሜ 1
37. ሆይበል አለምነህ፡- ዕድሜ 20
38. እግዜሩ አለማየሁ፡- ዕድሜ 16
39. አበበ እንዳላማሁ፡- ዕድሜ 30
40. አበባየሁ አሰፈራው፡- ዕድሜ 20
41. ቤዛዊት አበበ፡- ዕድሜ 10
42. ዳኛቸው ዘውዱ፡- ዕድሜ 16
43. ጠጅቱ ታደሰ፡- ዕድሜ 20
44. ገብረህይወት ብርሀኑ፡- ዕድሜ 35
45. ባንቻለም ግርማው፡- ዕድሜ 20
46. ደምለው ጌታ፡- ዕድሜ 30
47. ዝኑ ደምስ፡- ዕድሜ 22
48. ስንታየሁ ደምለው፡- ዕድሜ 10
49. አልማዝ ደምለው፡- ዕድሜ 1
50. ፈንታነሽ ምህረት፡- ዕድሜ 36
51. ጥላሁን ጤና አገኝ፡- ዕድሜ 24
52. ሀብታሙ ደሳለኝ ፡- ዕድሜ 34
53. አለሚቱ፡- ዕድሜ 20 (የአባት ስም ለጊዜው ያልታወቀ)
54. ሚጣ ሀብታሙ፡- ዕድሜ 6
55. አበበ ቦጋለ፡- ዕድሜ 26
56. አሸብር ከበደ፡- ዕድሜ 25
57. የውቤ ከበደ፡- ዕድሜ 34
58. ማስተዋል ነገሰ፡- ዕድሜ 21
59. አበበ አጥናፉ፡- ዕድሜ 32
60. አለምነሽ ሚካኤል፡- ዕድሜ 25
61. አቢ አበበ፡- ዕድሜ 1
62. ውብነሽ፡ ዕድሜ 23 (የአባት ስም ለጊዜው ያልታወቀ)
63. ሚጣ አስረስ፡- ዕድሜ 7
64. ሙላት ቦጋለ ፡- ዕድሜ 33
65. አዳነች፡- ዕድሜ 21 (የአባት ስም ለጊዜው ያልታወቀ)
66. አለነ ቦጋለ፡- ዕድሜ 25
67. አበበ ጌታቸው፡- ዕድሜ 36
68. ትግስት፡- ዕድሜ 20 (የአባት ስም ለጊዜው ያልታወቀ)
69. ፀጋዬ አበበ ፡- ዕድሜ 3
70. ብርቱካን አበበ (ዕድሜ ያልታወቀ)
71. ላቀች አይናለም፡- ዕድሜ 30
72. ይበሉሽ ወርቅነህ፡- ዕድሜ 7
73. የአቢዎት አዲሱ፡- ዕድሜ 40
74. ይነበብ ታከለ፡- ዕድሜ 17
75. አዳሙ ታከለ፡- ዕድሜ 15
76. ሀብለወርቅ ታከለ፡- ዕድሜ 13
77. ማንጠግቦሽ አለሙ፡- ዕድሜ 36
78. ፈንታነሽ አገኘሁ፡- ዕድሜ 16
79. ቢተው እንዳላማሁ፡- ዕድሜ 29
80. መምህር ንብረት ጋንቲ፡- ዕድሜ 30
81. ወይዘሮ እናት (የመምህር ንጋት ሚስት)

ከላይ በዝርዝር የተጠቀሱት በግፍ አማራ/አገው በመሆናቸው በአንድ ቀበሌ ብቻ የተገደሉት ናቸው። በሌሎች ቀበሌዎች ደግሞ ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸው ዜጎች ተገድለዋል። በመተከል የተፈፀመው ይህ ጅምላ ጭፍጨፋ ሕፃን ማፍረስ ከሚችል ዘመናዊ መሳሪያ እስከ ቀስት ድረስ የጦር መሳሪያዎች አገልግሎት ላይ የዋሉበት ነው። አስከሬን ለማንሳት ተከልክሎ እስከ 10 ቀናት ድረስ ሜዳ ላይ ወድቆ ቆይቷል። በመተከል ሴቶች ታግተው ይህ ዘገባ እስከተጠናቀረበት መስከረም 13 ቀን 2013 ዓ.ም. የተወሰዱበት አልታወቀም።

በአጠቃላይ ከወያኔ ጊዜም የከፋ ጭፍጨፋ በአማራ ላይ እየተፈፀመ ነው። ከደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ ወደ ትውልድ ቀያቸው ሲመለሱ በሽብር ቡድን የታገቱ የአማራ አዳጊ ተማሪዎች (ከ17ቱ ውስጥ አብዛኞቹ ሴቶች) የውሃ ሽታ ሆነው ቀርተዋል። ሕፃናትን ከሜዳ ላይ አግቶ ከነነፍሳቸው የሚገፈው አካግ ተማሪዎችን ምን ሊያደርጋቸው እንደሚችል መገመት አያዳግትም።



ገለታው ዘለቀ
(የባልደራስ ፅህፈት ቤትና ሕዝብ ግንኙነት ሓላፊ)



# የማንነት ፖለቲካ ምንነትና አደጋዎቹ

## ባህላዊ ማንነትን ፖለቲከኛ ስናደርግ ያመረትናቸው ችግሮች

የማንነት ፖለቲካ ይህን ስያሜውን ያገኘውና በሚታይ መልክ ብቅ ያለው በ20ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ ነበር። በዚሁ ወቅት የሴቶች ንቅናቄ፣ የጥቁሮች ንቅናቄ፣ የአካለ ስንኩላን ንቅናቄዎች፣ የብሔር ንቅናቄ በስፋት የታዩበት ጊዜ ነበር። የማንነት ፖለቲካ ወደ አካዳሚክ ዲስኩር የገባውም በዚሁ በቅርቡ ነበር።

የማንነት ፖለቲካ ስንልም በእነዚህ ማንነቶች ላይ የሚሰራ የፖለቲካ ቤት ማለታችን ነው። ወደዚህ ፖለቲካ የሚገቡ ሃይሎች ደግሞ የፕራይሞርዳያሊዝም ፍልስፍና አማኞችና ኢንስትሩመንታሊስቶች ናቸው ማለት ነው።

የማንነት ፖለቲካ በቡድን የወል ግብር፣ የወል ስብእና፣ የወል እሴት፣ የወል ቋንቋ፣ የወል መልክ ላይ የሚቆም የፖለቲካ ስልጣን ሩጫ ሲሆን ከማንነት ፖለቲካ ውስጥ አንዱ ቅርንጫፍ ደግሞ የብሄር ፖለቲካ ነው።

ሃይማኖታዊ ፖለቲከኛነት ከማንነት ፖለቲካ ጋር የተያያዘ በመሆኑም ዓለም ያሳለፈችበትን የፖለቲካ ሕይወት ስናይ በተለይ በሃይማኖት ላይ የተመሠረተ የሕዝብ አስተዳደር ቀደምትነት ያለው ሆኖ እናያለን።

ወደ ብሔር ፖለቲካ ስንመጣ እንደሌሎቹ የማንነት ፖለቲካዎች ሁሉ ማዕከላዊ ጉዳዮች ይኖሩታል። ከነዚህም ውስጥ የእውቅና ጉዳይና የሶሺዮ ኢኮኖሚክ ጉዳይ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ▶

በማንነት ፖለቲካ ውስጥ በተለይም የአሜሪካ የጥቁሮችን ንቅናቄ ስናይ፣ የሴቶችን ንቅናቄ ስናይ የእውቅና ጉዳይ ማዕከላዊውን ቦታ ይይዛል። በአንፃሩ የኢትዮጵያን የብሔር ተኮር ፖለቲካ ስናይ ከእውቅናም ባሻገር የሶሺዮ ኢኮኖሚክና ሌሎች እድሎችን በቀጥታም በህቡዕም ይዞ የመነሳት ፍላጎት ይታይበታል።

የማንነት ፖለቲካ የምንለው በእንግሊዘኛው Identity የሚል ስያሜ ያለው ሲሆን የመለየት (separation) ፖለቲካ ማለት ነው። ራሳችንን ከሌላው የሚለየንን ነገር በማውጣት በዚያ ላይ የሚቆም ፖለቲካ ማለት ነው። አይደንትቲ የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል ምን ያህል በሚመጥን መልኩ ተተርጉሞ ማንነት እንደተባለ አላውቅም። የማንነት ፖለቲካ ከሚባል የመለያ ፖለቲካ ቢባል የተሻለ ይመስላል። ለማናቸውም ግን ፖለቲካችን በአይደንትቲ ላይ ከቆመ በልዩነት ላይ ቆመ ማለት ሲሆን በዚህ ጊዜ በከፍተኛ ሁኔታ ዜጎች ራሳቸውን ከሌላው በሚለያቸው ነገር ላይ ትኩረት እንዲሰጡ የሚያደርግ ከባቢ ውስጥ እንገባለን። ቡድኖች ልዩነታቸውን ያጠብቃሉ። ልዩነት በጣም ሞቅ ያለ ጉዳይ ይሆናል ማለት ነው። ለምን ልዩነትን ይፈልገዋል? ለምን ያጎላዋል? ካልን አንዳንዱ በአሲምሌሽን ደንብሮ ሲሆን አንዳንዱ ደግሞ በብሄር ኢንተርፕሩነርስ እየተነዳ የሚሄድ ስለሆነ ነው። አሲምሌሽን ያስፈራው አካል ደንብሮ ጽንፍ ሄዶ የልዩነት ፖለቲካ አምጥቶ ራስን በራስ ማስተዳደር በየቤት ማደር እያለ ሲሰብክ እንዲሁም ደግሞ አንዳንድ የፖለቲካ ስልጣን ጥም ያላቸው ነገር ግን ተወዳድረው ማሸነፍ ሲያቅታቸው አቋራጭ የስልጣን መስመር አድርገው የሚያዩት ይህ የልዩነት ፖለቲካ በመሆኑ በዚያ ላይ ለመወጣጣት ስለሚጠቀሙበት ነው። ኢትዮጵያን መቃረጥ ይፈልጋሉ። በተለይ በብዙህ ሃገራት ውስጥ በኣንጻራዊነት የብሄር ፖለቲካን የሚፈልጉት ለሂቃን የሚነሱት ከሁለት ኣቅጣጫ ሲሆን በጣም ኣነስተኛ ብዛት ካለው ቡድንና ከፍተኛን ቁጥር ከሚይዘው የብሄር ኣባላት መካከል ሆኖ ይታያል። ይህ የሚሆንበት ምክንያት ኣነስተኛ ቁጥር ያለውን ቡድን ወክለው ማእከላዊ መንግስትን ለመቆጣጠር የሚሹት የብሄር ኢንተርፕሩነርስ የሚኖራቸው ድብቅ ኣጀንዳ በብዙሃኑ ዋጋ በቀላሉ ቡድናችንን መለወጥ እንችላለን፣ ቡድናችንን ካሳመጽነው ብዙሃኑን ስለሚፈራና ለውጥን ስለሚፈራ ኣጥብቆ ይደግፈንና ረጅም ዘመን እንገዛለን የሚል ሲሆን ብዙ ከሆነው ብሄር የሚወጡ ኢንተርፕሩነርስ ደግሞ ይህን ብዛት ይዘው ስልጣን ይገባኛል ለማለት ትልቅ የመከራከሪያ ሎጂክ ስለሚመስላቸው ነው። ቁጥሩን ይዘው በዚህ ቁመት ልክ ይገባኛል እያሉ መቆየቱ ወደ ስልጣን ያመጣናል ብለው ስለሚያምኑ ከዚህ ብዙሃን የሚወጡ ኢንተርፕሩነርስ ይህንን ግዝፈት ለስልጣን መወጣጫ ሊጠቀሙበት ስለሚፈልጉ የብሄር ፖለቲካ እንዲጠፋ ኣይፈልጉም። ወደ ስልጣን ለመሄድ መንገድ ያቀላል ብለው ያምናሉ። ብዛቱን ይዘው ፍረዱን ይላሉ። ያ ኣነስተኛ ቁጥር ያለው ስልጣን ላይ ካለ ደግሞ በብዙው የምጠቀመው ኣለ ብሎ ስለሚያምን እንዲሁ የብሄር ፖለቲካው ይጠቅመኛል ብሎ ኣለቅም ይላል። በዚህ መሃል ቁጥራቸው በመሃል ያሉ ወደ ስልጣን ያልመጡት ብሄሮች ደግሞ ብሄራዊነት ይሻላል፣ በኣይዲዮሎጂ ላይ ተመስርተን ወደ ስልጣን እንሩጥ የሚል ነገርን ማራገብ ይመርጣሉ። በኣጠቃላይ የብሄር ፖለቲካ በዚያም በዚህም ከፍትህ ጥያቄ ይልቅ የጥቂት የስልጣን ጥመኞች ኣቋራጭ መንገድ ተደርጎ ስለሚወሰድ በጣም ተወጋዥ ያደርገዋል።

በአጠቃላይ በአሁኑ ጊዜ በዓለማችን ላይ በማንነት ፖለቲካ ጐልተው የሚገለጹት የብሔር ፖለቲካና የሃይማኖት ፖለቲካ ሲሆኑ መንግሥታቸውን በሃይማኖት ማንነት ላይ ያቆሙ እንደ ሳውዲ አረቢያ ያሉ አገራት በቀደምትነት ይጠቀሳሉ። እነዚህ አገሮች ሃይማኖታዊ በሆነ ሕግ የአገሮቻቸውን ሕገ-መንግሥት የሚያስተዳድሩ ሲሆን ብዙ አገራት ግን መንግሥትንና ሃይማኖትን፣ ዘርን ወይም ብሄርንና ፖለቲካን ነጥለው ወደ ዘመናዊ አስተዳደር ተሻግረው ይታያል። ወደ ብሔር ፖለቲካ ስንመጣ በአንዳንድ አገራት ለምሳሌ ሕንድና ኔፓል እንዲሁም በተወሰነ ደረጃ ኢንዶኔዥያ የሚታይ ሲሆን በብሔር ፖለቲካ ውስጥ ደፍሮና ጠልቆ የገባ እንደ ኢትዮጵያ የለም። ኢትዮጵያ ከሌሎች አገራት በተለየ መንገድ በጥልቀት የብሔርን ፖለቲካ የምታራምድ አገር ናት። የብሄር ፖለቲካዊ ማንነት እስከ መገንጠል የሚሄድባት አገር በዚህች ፕላኔት ላይ ኢትዮጵያ ናት። ኢትዮጵያ ወደዚህ ፖለቲካ በመምጣት ያተረፈችውንና ያጣችውን እያነሳን ከመወያየታችን በፊት በአጠቃላይ የብሔር ፖለቲካ ምን ተፈጥሮ እንዳለው እንይ።

የብሔር ፖለቲካ የማንነት ፖለቲካ ነው ስንል በተለይ ብዙህ በሆኑ አገሮች ብሔሮች በባህላዊ ቡድነኝነት ላይ የተመሠረተ የፖለቲካ ድርጅቶችን ይመሠርቱና በዚህ ባህላዊ ማንነት ላይ ለዚህ ባህላዊ ማንነት ጥላ ሆነው የሚቆዩበት ጠገግ ነው። በርግጥ ፖለቲካ ምንጊዜም ቢሆን ከማንነት አይወጣም። ብሔራዊ አጀንዳ ይዞ የሚመሠረት የፖለቲካ ድርጅትም ያው ብሔራዊ ማንነትን እንደ ማንነት መገለጫው አድርጎ ነው የሚቆመው። ጥያቄው ፖለቲካ ከአካባቢ ማንነት ወደ ሃገራዊ ማንነት ማደግ አለበት ነው።

የብሔር ፖለቲካ ችግር የቡድንን ማንነት እንደማይለወጥ አልፋና አሜጋ ማየቱ ነው። ይሁን እንጂ ብዙ ብሔር ባለበት አገር አንድ ብሔር የራሱን ቡድን ልዩ ቋንቋ ሲናገር በማየቱ ለይቶ ቢያየውም ሁዋላ ወደ ውስጥ ማየት ሲጀምር ማይክሮ ማንነቶች መታየት መጀመራቸው አይቀርም። ከብሔር በታች ያሉ ጎሳ እንበለው ወይም ሌላ እንበለው ሌሎች አነስተኛ ክፍፍሎች መድመቅ ይጀምራሉ። የመልክዓ ምድር ክፍፍሎች፣ የአነጋገር ዘየዎች ሳይቀሩ ለብቻ ስንሆን ልዩነት ሆነው መውጣታቸው አይቀርም። በመሆኑም የልዩነትን የመጨረሻ ቅንጣት ፍለጋ ያንከራትተናል። ለዚህ ነው ዘመናዊ ዴሞክራሲ በሰው ልጆች ልዩነት የመጨረሻ ቅንጣት በሆነው የግለሰብ ልዩነት ላይ መመሠረት ይሻላል ብሎ የሚያምነው። በግለሰቦች መብት ላይ ያተኮረ ከዚያም ቡድኖችን የሚንከባከብ የፖለቲካ መሠረት መፍጠሩ መንግሥት የገዛ ህዝቡን ለመድረስና ለመርዳት ቀና መንገድ ይሆንለታል። እንደ ኢትዮጵያ ባለች አገር ውስጥ ልዩነትን እናንሳ ካልን ከብሔር በላይ ነገድ አለ። ከዚያም ደግሞ ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምስራቅ፣ ምእራብም ልዩነትን ሊሰሩልን ይችላሉ። ከፈለግን።

በሳይንሳዊ ክፍፍል የዘር ቆጠራ የናይሎ፣ የኩሽ፣ የሴምና የኦሞ ቋንቋ ተናጋሪዎች ነን። ወደ ታች ደግሞ በብሔር ከዚያም ጎሳ እያለ የደም ሃረግን ተከትሎ ይወርዳል። በብሔር ላይ የፖለቲካ ቤትን ለመሥራት የሚያስችል የፍልስፍና መሠረቱ ብዙ ግልጽ አይደለም። አንዳንዶቹ ብሔርን ከደም ሐረግ ጋር በማያያዝ ቡድኖች በብሔር ላይ የተመሠረተ የፖለቲካ ጨዋታ ቢያደርጉና ፌደራሊዝም በዚያ ቢቀረጽ አስተዳደሩ ትጋትንና ርኅራኄን ተግባቦትን ያመጣል ከሚል ይመስላል። ችግሩ ግን ማይክሮ ማንነቶች ማለቂያ ስለሌላቸው ይህ ፍልስፍና ትርጉም እንዲያጣ ያደርገዋል፡ ፡ በአጠቃላይ ስናይ የብሄር ፖለቲካ በሁለት ይከፈል ይመስላል። አንደኛው ፕሪሞርዲያሊዝም ሲሆን ይህ ኣስተሳሰብ ብሄርን የደም ሃረግ ውጤት አድርጎ ያያል። የብሄሩን አባላት የሚያስተሳስረው ውጪያዊ የሆነው ባህልና ቋንቋ ብቻ ሳይሆን የስነ ህይወት ትስስር ጉዳይ አለ ብሎ ያምናል። በዚህ ፍልስፍና ላይ የሚቆም የብሄር ፖለቲካ የፕሪሞርዲያሊዝም እምነት የሚከተል ነው ማለት ነው። በሌላ በኩል በብሄር ላይ የተመሰረተ ፖለቲካ ባህልንና ቋንቋን እንደ ማንነት መገለጫ ኣይቶ በነዚህ ልዩነቶች ላይ የፖለቲካ ቤቱን ሰርቶ ነገር ግን ብሄርን የደም ትስስር ውጤት ኣድርጎ ኣያይም። የፕሪሞድሪያሊዝም ተቃራኒ የሆነው አስተሳሰብ ብሄርን ማህበራዊ ስሪት ወይም ሶሻሊ ኮንስትራክትድ ነው ብሎ ያምናል። ይሄ እምነት ብዙ የዓለም ምሁራንንና ፖለቲከኞችን ይገዛል። ይህ ማለት አንድ ሰው እናትና ኣባቱ ኦሮሞ ሆነው ትግራይ ውስጥ ተወልዶ ቢያድግና ትግርኛ ቢናገር የትግራይ ብሄር ይሆናል ማለት ነው። ማንነት የሚገጸው በዘር ሳይሆን በቋንቋና ባህል ነው። በዚህ አገባብ ብሄር የፖለቲካ ጽንሰ ሃሳብ ነው ማለት ነው። በኢትዮጵያ ሁኔታ ስናይ ግን የብሄር ፖለቲካው የተመሰረተው በፕራይሞር ዳያሊዝም ኣስተሳሰብ ነው። ስለሆነም የብሄር ፖለቲካ ወይም ብሄር በኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ ጽንሰሃሳብ ሳይሆን የማይነካ የማይገሰስ የደም ሃረግ ጨዋታ ነው ማለት ነው።

ኢትዮጵያ እንግዲህ የፖለቲካ መሠረቶቿን ያደረገችው በዚህ ከላይና ከታች ልዩነትን ►

በከላና በአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ላይ በቆመ የፖለቲካ መሠረተ ላይ ሲሆን ኢትዮጵያ ከሌሎች አገሮች ማለትም የብሔር ማንነትን ወደ ፖለቲካ ካስጠጉ አገሮች የምትለየው ከብሄር ፌደራሊዝሙ ባሻገር የብሄር ፖለቲካን በማስተናገዷ ነው። ለዚህ ነው እንደ ኢትዮጵያ የብሔር ፖለቲካን ጠልቆ የገባበት አገር የለም የሚያስብለን። ለምሳሌ ስዊዘርላንድን ብንወስድ አስተዳደሯ ለቋንቋ ትኩረት የሰጠ ሲሆን ነገር ግን የፌደራል ስርዓቷ በካንቶኖች የተከፋፈለ ነው። ስዊዘርላንድ ውስጥ አራት የቋንቋ ኮሚኒቲዎች ያሉ ሲሆን አስተዳደሯ ግን በሃያ ስድስት ካንቶኖች ወይም ስቴቶች የተዋቀረ ነው። ገዢ ፖለቲካዋም በብሄራዊ ማንነት ላይ የተመሰረተ በስዊዝ ማንነት ላይ የተመሰረተ ነው። በአንፃሩ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ማንነት ያላቸውን ፓርቲዎች ከውጪ በሪዘርቭ አስቀምጣ ዋናውን የፖለቲካ ሜዳ የያዙት የብሔር ፖርቲዎች ናቸው። በኢትዮጵያና በስዊዘርላንድ መካከል ያለው ዋና መሰረታዊ ልዩነት የስዊዘርላንድ ቡድኖች ለስዊዝነት የሰዋቸው ጉዳዮች አሉ። ከነዚህም ውስጥ ፖለቲካዊ ማንነትና ግዛት ናቸው። እነዚህን ሁለቱን ስዊዝ የወሰደችው ሲሆን ከዚያ በመለስ ያለውን ቋንቋና ባህልን ግን ቡድኖች ጠብቀው ይኖራሉ። ኢትዮጵያ በአንጻሩ ለኢትዮጵያዊነት ያስቀረችው ቁምነገር የለም። ፖለቲካዊ ማንነት፣ ግዛት፣ ታሪክ፣ ቋንቋ ፣ባህል ሁሉ በየቡድኑ የተያዙ ናቸው። ለኢትዮጵያዊነት እንደስዊዝ የሰዋነው ባለመኖሩ ነው ትልቁ ልዩነት።

ሕንድ አገር በርግጥ አንዳንድ በማንነት ላይ የቆሙ አካባቢያዊ ፓርቲዎች ቢኖሩም ሥልጣኑን የያዘው በብሔራዊ ማንነት ላይ የተመሠረተ ፓርቲ ነው። ጥቂት የሆኑት የብሔር ፓርቲዎች ከኢትዮጵያ በተቃራኒው ከውጪ በተጠባባቂነት የተቀመጡ ተፅዕኖ የሌላቸው ናቸው። እንዴውም ህንድ አሁን ከማጠፋቸው ራሱ ጊዜ እየጣላቸው ይሄዳል ብላ ለጊዜው ችላ ያለቻቸው ነው የሚመስሉት።

የኢትዮጵያ የብሄር ፖለቲካና ፌደራሊዝም ከውስጥ ወደ ውጭ ሲታይ

የብሄር ፖለቲካ ዓለማቀፋዊ ቢሆን ዓለም ምን ትሆናለች?

በአጠቃላይ ዓለም በተለይ የብሄር ፖለቲካን ከሰፈሯ አርቃ ነው የሚታየው። ርግጥ ነው በጥንት ጊዜ የፖለቲካ ርእዩት ባልዳበረበት ጊዜ ዓለም በጎሳና በነገድ አስተዳደር ስር ቆይታለች። ይሁን እንጂ የአሁኗ ዓለም ከጎሳ ይልቅ በርእዮት ላይ የተመሰረተ ፖለቲካና ዴሞክራሲ ስለማረካት ይህንን ፖለቲካ ትታው ይታያል።

እስቲ እንደዚህ እናስብ። ከፍ ሲል እንዳልነው የብሄር ፖለቲካን አለማቀፍ እናድርገው እስቲ። በእንበል ገበያ ውስጥ እንሁንና የዓለም ሃገራት የኢትዮጵያን የፖለቲካ ተመክሮ ወስደን በብሄር እንደራጅ ቢሉ ዓለም ምን ትሆናለች? ብለን እንጠይቅ። ዓለም የብሄር ፌደራል ስርዓትን ልከተል ብትል፣ በየብሄሯ በየቋንቋዋ ፖለቲከኛ መሆን ቢያምራት ዓለም ትፈርሳለች። ሃገሮች ሁሉ ይፈርሳሉ። የብሄር ፖለቲካ ዓለምን ያፈርሳል። ሩቅ ሳንሄድ አህጉራችንን አፍሪካን ስናይ አንድ ቋንቋ የሚናገሩ አፍሪካውያን በሁለትና በሶስት የአፍሪካ ሃገር ተበትነው ይታያል። ለምሳሌ የኪንያሩዋንዳን ቋንቋ የሚናገሩ ማህበረሰቦች በሩዋንዳ፣ በዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎና በኡጋንዳ ይገኛሉ። አፍሪካ እንደ አህጉር 3000 የሚገመቱ ብሄሮች ያሏት ሲሆን በአማካይ 56 ብሄር በአንድ የፖለቲካ ጠገግ ስር ሰፍሯል ማለት ነው። አፍሪካ በብሄር ፖለቲካ ውስጥ ብትገባ ወይም ወደየ ብሄሯ ማሽጋሸግ ብትፈልግ አህጉሪቱ ትፈርሳለች ብቻ ሳይሆን ፈርሳም አገር አትመሰርትም። የብሄር ፖለቲካን በዓለም አደባባይ ላይ ስናየው ዓለምን የሚያፈርስ ሲሆን በኛ አገር ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ በገዛ ቤታችን ውስጥ ያመጣብንንና ሊያመጣብን የሚችለውን ችግር ዝቅ ሲል እንመልከት። በዚህ ዘመን የብሄር ፖለቲካን እንከተል ስንል የሚከተሉትን ችግሮች እናተርፋለን። ሚዛናዊ ለመሆን ያሉትን ጥሩ ጎኖችም እንዘረዝራለን። በመጀመሪያ ከሚበዛው አሉታዊ ጎኑ እንነሳ።

አሉታዊ ጎኖቹን አንድ ሁለት እያልን ከማንሳታችን በፊት እስቲ አንድ ዝንባሌ የሚስብ ጥያቄ በአረማሞ እናንሳ። ጥያቄው ይህ ነው። የሰውን ልጅ ማንነቶቹን ሁሉ ፖለቲከኛ ስናደርግበት ሰው ምን ይሆናል? ምን ዓይነት ማህበር ይመሰርታል?

## የሰውን ሁለንተናዊ ማንነት ፖለቲካዊ ስናደርግ ምን ችግር ይገጥመናል?

የሰው ልጅ የተደራራቢ ማንነቶች ውጤት ነው። ይህ ማንነቱ ግለሰቡን ከግለሰብ ማንነቱና ከቡድን ህይወቱ አንጻር ይገልጻዋል። በሃገር ጥላ ስር የሚሰፍሩ ዜጎች በጉልህ ከሚገልጷቸው የቡድን ማንነቶች መካከል ሃይማኖት፣ ብሄር፣ ጎሳ፣ መልክዓምድር የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ። ታዲያ የሰው ልጅ ሃገራዊ ማህበር ሲመሰርት ይህንን ማንነቱን ሁሉ የፖለቲካ መደራጃ ቢያደርገው ምን ይሆናል? የሚለው ጥያቄ በጣም መሳጭ ነው። ዜጎችን ባህላቸውን፣ ቋንቋቸውን፣ የተወለዱበትን አካባቢ፣ እሴቶቻቸውን ሁሉ ፖለቲከኛ ብናደርግባቸው መጀመሪያ የምናጠፋው ይህንን ማንነታቸውን ራሱን ነው። ከዚያ ሲለጥቅ ደግሞ ወደ ጎን ከሌሎች ማንነቶች ጋር ግጭትን እንዲያመርቱ እናደርጋቸዋለን:: ከዚያ ሲለጥቅ ደግሞ ለዋናው ማህበራቸው የጋራ ማንነት እናሳጣለን:: ከዚያ ሲለጥቅ ደግሞ የዋናውን የህብረት ቤታቸውን ወይም የሃገራቸውን የፖለቲካ ጨዋታ ሴማ እናሳጣዋለን። አንድ ሃገር ስብስብ የተባለን ሁሉ ፖለቲከኛ ማድረግ ቢፈልግና ብሄርን፣ ሃይማኖትን፣ ብሄራዊ ማንነትን፣ ጂኦግራፊን፣ ነገድን ሁሉ ለፖለቲካ ቤት መስሪያነት ቢፈቅድ ያ ሃገር የሚፈጥረው የፖለቲካ መስመር ምርጫውን ያበላሻል። ሃገራችን ኢትዮጵያ ከሰውነቶቻችን መሃል ፖለቲከኛ እንዳይሆን የከለከለችው ሃይማኖታችንን ብቻ ነው። በሃይማኖት ላይ መደራጀትን በህገ መንግስት ከልክላለች። የኢትዮጵያ ህገ መንግስት ኣንቀጽ 11 ይህንን ይደነግጋል። ከዚህ ውጭ ግን ብሄርን፣ መልክዓምድርን፣ ብሄራዊ ማንነትን ወይም ኢትዮጵያዊነትን፣ ነገድን፣ ጥምረትን፣ ሃሳብን ሁሉ መሰረት ኣድርጎ ፖለቲካ መጫወት ይቻላል። ይህ ደግሞ እጅግ ብዙውን የሰውን ማንነት ፖለቲከኛ ከማድረጉም በላይ በዚህ ዓይነት ኣሰላለፍ ሃገራዊ ራእይ ማየትና ሃገራዊ ምርጫ ማሰብ ለጋራ ቤት ኣብሮ መስራት የማይታሰብ ነው። ሃገር የሚባለውን ትልቅ ማህበር ስንፈጥር ከሚኖሩት ስብስቦች መካከል ፖለቲከኛ የምናደርገውን መምረጥ ኣለብን። ዓለም ካሉት ስብስቦች መካከል ብሄራዊ ማንነትን ለፖለቲካ መደራጃነት ይፈቅድና ሌላውን ማለትም በብሄር መደራጀትን፣ በሃይማኖት መደራጀትን፣ በመልክዓምድር መደራጀትን ወዘተ ይከለክላል። ኢትዮጵያ ብዙውን ማንነታችንን ፖለቲሳይዝ ማድረጓ ያመጣብን ችግር ሃገራችን ወደ መድብለ ፓርቲ ስርዓት እንዳትሻገር ከማድረጉም በላይ ለምርጫ እንዳንመች ለቅንጅት እንዳንመች ኣድርጎናል። የሰውን ሁለንተና ፖለቲከኛ ካደረግንበት የምናጋጨው ነገር ብዙ ነው። ፖለቲካ በተፈጥሮው ግጭትን የያዘ ነው። በፖሊሲ መጋጨት፣ እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ማለት በፖለቲካ ውስጥ ጤነኛ ነገር ነው። አንዱ ፓርቲ ከሌላው የተሻለ ፖሊሲ እንዳለው እያሳየ ሌላውን እያኮሰሰ በማሳየት ነው ለምርጫ የሚሮጠው። በመድብለ ፓርቲ ስርዓት ውስጥ ይህ እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ጨዋታ መልካም ነገር ነው። የፖለቲካ ወጉም ይሄ ነው። ነገር ግን ይህ የመድብለ ፓርቲ የፖለቲካ ጨዋታ ወደ ብሄር ማንነት ሲሄድና ብሄርን ፖለቲከኛ ስናደርግ በቀጥታ ግጭቶችን ወደ ብሄር እናወርዳለን ማለት ነው። ብሄር ፖለቲከኛ ሲሆን በብሄሮች መካከል እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ግጭትን እናመጣለን ማለት ነው። ይህ ችግር በጣም ኣደገኛ የሆነ ችግር ስለሚያመጣ ማህበራችንን ይበጠብጣል። ስለዚህ ነው ማንነትን ፖለቲከኛ ስናደርግ የማህበራችንን መንጋ ይበትናል የሚያስብለን። ከማንነቶች መካከል ብሄራዊ ማንነትን ለፖለቲካ መደራጃነት መርጦ ሌሎቹን ማንነቶች በራሳችሁ ምህዋር ላይ ዞሩ ማለት ዴሞክራሲያዊና የመድብለ ፓርቲ ስርዓት መርህ ነው። እኛ በአንጻሩ ማንነትን ሁሉ ለፖለቲካ መደራጃነት ስንፈቅድ የወጣልን ዴሞክራቶች የሆንን መስሎን ከሆነ ተሳስተናል። ስለዚህ ማንነቶችን ሁሉ ፖለቲከኛ ከማድረግ መውጣት ያስፈልጋል።

# የደም ካባ




ውቤ ደነቀው መኮንን

**ውድ ኢትዮጵያዊያን ወገኖቼ**

‹‹ ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም›› የተሰኘው አባባል ዛሬ እውን ሆኖ አይተናል። በሰሞነ ጳጉሜን መስከረም ሊጠባ አምስት ቀናት ሲቀሩት ድፍን የኢትዮጵያን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን መላው ዓለምን በዘግናኝና ሰቅጣጭነቱ ጉድ ያሰኘው የሰኔ ሃያ ሦሥቱና በተከታታይ ቀናት የተካሄደውን የዘር ማጥፋትና የንብረት ውድመት ወንጀል እንደመሩ የሚነገርላቸው ካባ ተሸለሙ ወደር የማይገኝለትን ኢትዮጵያዊውን ናዚ የክብር ካባ የሸለመው ኢህዴን/ብአዴን/አዴፓ/ብልፅግና /ኢህአዴግ/ ስለሸልማቱ ምን ምክንያት ደርድሮ ይሆን?

ተሸላሚው አቶ ሽመልስ አብዲሳ በኦህዴድ/ኦዴፓ/ብልፅግና/ኢህአዴግ ወደ ቁንጮ አመራርነት ጎልተው ከወጡና ኦሮሚያ ተብሎ በትህነግ/ኢህአዴግ የተሰየመው የሀገራችን ክፍል መሪ ከሆኑ በኋላ እኩይ ተግባራት መፈጸማቸው ብዙዎች ሲናገሩ ይደመጣሉ። በሰብአዊ ፍጡራን ላይ የተፈፀሙት ድርጊቶች ጤነኛ አዕምሮ ያለው ማንኛውም ጨካኝ የሚባል ሰው ሊሠራው ከሚችለው በላይ አስከፊ ናቸው። ለማሰብም ይከብዳሉ። አስከፊነታቸውን ለመግለፅም ምድራዊ ቃላት አይበቃቸውም። ይህንን ስል የቃላትን የመግለፅ አቅም ዝቅ ማድረጌ አይደለም። ቃላት በጠቢባኑ በተለይም በባለቅኔዎች ዘንድ እጅግ ከፍተኛ የመግለፅ አቅም አላቸው። በመንግሥታዊ ድጋፍ ሰው በስለት ሲታረድ፣ ሰዎች የሞተ ቤተሰባቸውን አስክሬን እንዳያነሱ ሲከለከሉ፣ የሟች ስጋ በየመንገዱ ተዘልዝሎ ደሙ ሲፈስ፣ የአስከሬን ዓይን ተጎልጉሎ እንዲወጣ ሲደረግ፣ አስክሬን በእሳት ሲቃጠል. . . በተጎጂዎች ላይ የሚፈጥረውን ስሜት ለመግለፅ ቀርቶ በትክክል ለማወቅም ያስቸግራል።

አንድ ዓመት ወደ ኋላ እንመለስ። ኢትዮጵያውያን በተለይም ደግሞ የአዲስ አበባ ነዋሪ በሚገባ ያስታውሰዋል። ዕለቱ በአዲስ አበባ ኢሬቻ የተባለው የጣኦት አምልኮት በዓል እንደሆነ የሚነገርለት የሚከበረበት ቀን ነው። የአሁኑ ካባ ተሸላሚ እንዲህ አሉ። ‹‹ከአንድ መቶ ሃምሳ ዓመት በፊት በዚህ ስፍራ የሰበሩንን ነፍጠኞች እነሆ ዛሬ ሰብረናቸዋል!



የሀገሪቱን መዲናም ተቆጣጥረነዋል።›› ይህ ንግግር አቶ ሽመልስ አብዲሳ ማናለብኝነታቸውን ለመላው ኢትዮጵያውያን ያወጁበት የመጀመሪያው ዕለት ነው። በወቅቱ በመስቀል አደባባይ የታደሙት የብአዴኑ ባለሥልጣን አቶ ላቀ አያሌው ለንግግሩ ያላቸውን አድናቆት ከተሰብሳቢዎቹ ጋር አብረው በማጨብጨብ ገለፁ። ቀጥሎም የተነሳውን ሕዝባዊ ቁጣ መሸከም ሲያቅታቸው ‹የኦሮምኛ ንግግሩ በወቅቱ አልገባቸውም። በመድረክ የተሰበሰበው ሰው ሲያጨበጭብ ልማድ ሆኖባቸው ነው ያጨበጨቡት› የሚል ማስተባበያ ፓርቲያቸው በስውር ባሰማራቸው የፌስቡክ ሰራዊት አባላት በኩል አስነገሩ። ይሁን፤ በመናጆነት ማጨብጨባቸውን በቅል ልቦና እንቀበለው። በማይገባቸውና በቋንቋቸው በማይዘጋጅ መድረክ ላይ ለምን ታደሙ? ግድ የለም ይሄም ለመንግሥታዊ ፕሮቶኮል ማለትም ለታይታ ብቻ ነው የተገኙት ይባል። ይህንን ንግግሩን ወደ ተግባር እየመነዘረ እወክለዋለሁ የሚሉትን የአማራን ሕዝብ ብሎም መሪዎችን እያስጨፈጨፉ ያሉት ሰው የሰላም አምባሳደር አድርጎ መሸለሙስ ከምን የመነጨ ይሆን? ይሄስ ባለማወቅ ሽመልስ አብዲሳ ከአርበኛ መሳፍንት ተስፉ ጋር ተመሳስሎባቸው ያደረጉት ይሆን?

ድርጊቱ የማይገርመን፤ ሚስጥሩም የሚገለጥልን የብአዴንን አመሰራረት ወደ ኋላ ተመልሰን ስናጤን ነው። በኢሕዴን ሦስተኛ ድርጅታዊ ጉባዔ በ1986 ዓ.ም. የፀደቀው የብአዴን ፕሮግራም እንዲህ ይላል፡- ‹‹ለረዥም ዓመታት ተንሰራፍቶ የኖረው ፀረ ሕዝብና ፀረ ዴሞክራሲ የነፍጠኛ ስርዓት ቀድሞ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ የተለያዩ ሕዝቦች በየአካባቢያቸው ለዘመናት ይተዳደሩባቸው የነበሩትን ነፃ መንግሥታት በኃይል አፍርሶና ረግጦ በአንድ ማዕከላዊ መንግሥት ስር በማስገባት ነው። . . . ከአማራው ብሔር እየተወለዱ በሥልጣን ላይ ሲቀያየሩ የኖሩት የዚሁ ስርዓት ገዥዎች ጭቆና እና ብዝበዛቸውን የሚያካሂዱት መንታ ስለት ባለው የአገዛዝ ዘዴያቸው ነበር።›› ብአዴን በዚህ መልኩ አማራ ጠል በሆኑና ከአማራው ሕዝብ ባልተወለዱ ሰዎች የተጠቁው ሕዝብ ወኪል ሆኖ የተመሰረተ ተቋም ነው። የዛሬወቹ ወንጀለኛን ሸላሚ አመራሮችም በዚህ መንገድ የመጡ ናቸው።

ሽመልስ አብዲሳ በዚሁ በያዝነው ዓመት ▶

ጥቅምትና ህዳር ወር ላይ በጃዋር መሐመድ «ተከብቤአለሁና ጠባቂዎቼ ተነሱብኝ» በሚል ሰበብ ከ86 በላይ ንፁሀን ዜጎች በላይ በአሰቃቂ ሁኔታ ግድያዎች ሲፈፀሙ፣ በበሽታና በእድሜ መግፋት ምክንያት እቤት የዋሉና የአልጋ ቁራኛ የሆኑ እና ዐይነሥውር አዛውንቶችን ጨምሮ ከመግደልም በዘለለ የተለያዩ የአካላቸውን ክፍል በመቆራረጥና በአውራ መንገድ ላይ በመጎተት ፎቶ ግራፍ መነሻ ሲደረግ፣ የአንድ ሳምንት አራስ/እመጫት በህፃናት ልጆቿና በቤተሰቧ ፊት ስትታረድ! ተባባሪ እንደነበሩ ይነገራል።

ይህ ሁሉ የግፍ ግድያ በሚፈፀምበት ወቅት የክልሉ ፖሊስ ለወንጀሉ ተባባሪ በሚመስል ሁኔታ ቆሞ የወንጀል ተመልካች ከመሆን ይልቅ ህግ ቢያስከብርና ሊከሰት የሚችለውን ጥፋት ለማስቀም «ትእዛዝ አልደረሰኝም» ባለበት ሁኔታ

በወቅቱ የክልሉ ፖሊስ አዛዥ የነበሩት ባለሥልጣን ጃዋር የኦሮሞ ሕዝብ ዓይን ነው እንጠብቀዋለን ማለታቸው አይዘነጋም አቦ ሽመልስ አብዲሳ የክልሉ የበላይ የሕዝብ አስተዳዳሪና እረኛ ሆነው ሳለ ይህን ሁሉ የግፍ ግፍ ተግባር ሲፈጸም « ጉሽ አበጃችሁ » ያሉ በሚመስል መንገድ ውንብድናውን አለማስቆማቸው የተሰጣቸውን የሥልጣን ሓላፊነት አለመወጣታቸውን ያሳያል። እኝህ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን የሚቾቹ ወኪል ነኝ በሚለው ብአዴን መሸለማቸው በብዙዎች ዘንድ እጅግ አሳዛኝና አስገራሚ ክስተት ሆኗል።

ይህ ከላይ የተዘረዘረው እንዳለና እንደተጠበቀ ሆኖ ሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም. ምሽት ላይ የተከሰተውን የአርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሳን «ባልታወቁ ሰዎች» መገደልን ተንተርሶ ከሥርዓት የወጣ የተቃውሞ ሰልፍ ተደረገ።

የኦሮሞ ተወላጆችን ጨምሮ ከሦስት መቶ ያላነሱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አማኞች ታረዱ። በእምነትና በዘር ማንነታቸው ብቻ ያለ አንዳች ሌላ ጥፋት ዜጐች በስም ዝርዝር ተለይተው በአሰቃቂ ሁኔታ ተገደሉ። የእያንዳንዱ ታራጅና ተገዳይ መኖሪያ ቤትና የንግድ ቤት አድራሻ በቅድሚያ በተጠና ሁኔታ የዘር ማጥፋትና የንብረት ማውደም ተፈፀመ። ይህ በተከናወነበት ሁኔታ ገዳዮቹ (ፅንፈኛው ቄሮ) የሀጫሉን መገደል መቃወምና ሀዘናቸውን መግለፅ መብታቸው መሆኑን በይፋ በመደበኛው የመንግሥትና የግል መገናኛ ብዙኀን አቶ ሽመልስና ሌሎች የክልሉ የበታች ሹሞቻቸው አወጁ። በዚህ የልብ ልብ የተሰማው አሸባሪው ቄሮ አዲስ አበባ ውስጥ መኖሪያ ቤቶችን ሰብሮ በመግባት ጭምር ከዱላና ድንጋይ እስከ ቦንብ የታገዘ ጥቃት አደረሰ። በመኪኖችና በህንፃዎች ላይም እንዲሁ ውድመት አካሄደ።

በ2012 ዓ.ም የግማሽ ዓመት የእቅድ አፈፃፀምና የቀሪውን ግማሽ ዓመት እቅድ ለክልል ምክር ቤታቸው ባቀረቡበት ወቅት ሾልኮ የወጣውና ከሰባት ወራት በኋላ በመምህር ዘመድኩን በቀለ ዩ ቲዩብ አማካኝነት ይፋ በተደረገው በሽመልስ አብዲሳ ንግግር ውስጥ የተደመጡት ሃሳቦች ዘግናኞች ናቸው።

1. ብታምኑም ባታምኑም ቄሮን ያደራጀነው እኛ ነን!
2. እኔ ራሴ ቄሮ ነኝ!
3. ቄሮ ተነስ ሰንለው የሚነሳ፤ ተበተን ስንለው የሚበተን እኛ የሰራነው ቡድን ነው!
4. ፖለቲካ ተንኮል ነው። ከውስጡ ሌላ ነገር የለውም። ስለሆነም የፖለቲካ ባለፅድል ለመሆን ጨዋታው ምን ያህል ተንኮል መስራት ትችላለህ ነው?
5. ፖለቲካ ቁማር ነው። ባግባቡ ቁማሩን የቆመረ አሸናፊ ይሆናል።
6. እኛም ይህን የቁማር ጨዋታ በሚገባ የተጫወትን በመሆኑ ዓባይን ተሻግረን ሄደንም ብዙ ሥራ ሠርተናል።
7. የቻልነውን አግባብተን (convince) አድርገን፣ ያልቻልነውን አደናግረን (confuse) በማድረግ በሚገባ የቁማሩን ጨዋታ ተጫውተናል።

በማለት በዕብሪት ዓባይ ማዶ (በአማራ ምድር) ሰው እንደሌለ ብቻ ሳይሆን የእሱን የተንኮል ፖለቲካ ጨዋታ ሊረዳና ሊያከሽፍ

የሚችል የፖለቲካ ስብዕና እንደሌለ በግልፅ ተናገሩ። ታዲያ ይህንን ሰው በሀገርና ወገን ወዳዱና በኩሩው የአማራ ሕዝብ ስም የክብር ካባ ሲያለብሱ ምን ተሰምቷቸው እንደሆን የሚያውቁት ሸላሚዎቹ ራሳቸውና አንድዬ ብቻ ነው። ሆኖም ካባው በተውልድ ውስጥ የደም ካባ ሆኖ ይቀጥላል።

በእኔ አረዳድ ከመጀመሪያው የነጃዋር መሐመድ ‹ተከብቤያለሁ› እልቂት ጀምሮ አስከ የሰባሪ ተሰባሪ ትርክት መመሪያ መሰል ንግግር ሰበብ ያለቁትንና የተጨፈጨፉትን፣ የታረዱትን፣ አካል ጉዳተኛ እንዲሆኑ የተፈረደባቸውን፣ መጠለያ አልባና የእለት ጉርስ እንዳይኖራቸው ሀብት ንብረታቸው ሆነ ተብሎ በጠላትነት መንፈስ የወደመባቸውን የአማራና የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች «እንኳንም አስጨፈጨፍከልን፣ እንኳን አሳረድክልን እንደማለት ነው። የቆሰለውም ሆነ ቤት ንብረት አልባና የእለት ጉርስ ለማኝ መደረጉ ለኛ ምናችንም ስላልሆነና እጅግም ስላሰደሰትከን ይህን የክብር ካባ ስናለብስህ ለሠራህቸውና ወደፊትም ለምትሠራቸው ተግባራት በሰፊው የአማራ ‹ክልል› ሕዝብ ሥም እውቅናና አድናቆታችንን እንገልጻለን። በአማራዋ መዲና በውቧ ባሕር ዳር ተገኝተህ ሽልማቱን ስለተቀበልከንም ለጥ ብለን እጅ እንነሳለን።» የሚል የተንበርካኪነት ድርጊት ነው።

እውነቱ ከላይ የተዘረዘረው ብቻ አይደለም። ሌሎችም አሉ። በተደጋጋሚ ንግግሮቻቸው ከሚደሰኩሩልን ሕዝብን የናቁ አቀራረቦቹ ተነስተን ፀረ አማራና ፀረ ኦርቶዶክስ የሆነውን ፅንፈኛውን ቄሮ የወንጀለኛ ስብስብ ራሳቸው ጭምር እንዳዋቀሩ መረዳት ይቻላል። ለዘር ማጥፋት ወንጀሉም ሆነ በሰበብ አስባቡ ደሀውን ሕዝብ እያፈናቀሉ መጠለያ አልባ እንዲሆንና የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ ለማኝ እንዲሆን የማፈናቀሉን ሥራ የሚመሩት እራሳቸው ሽመልስ አብዲሳ ለመሆኑ በራሳቸው አንደበት ተናግረዋል። ለቁጥር በሚያታክት ድግግሞሽ የገለጹና ማስረጃም የሰጡ በመሆኑ የ‹ክብር› ካባ ሽላሚዎቹን ጨምሮ በሰብአዊ መብት ጥሰትና በዘር ማጥፋት ወንጀል ሊጠየቁ ይገባል። በዓለም አቀፍ ደረጃ የዘር ማጥፋት ወንጀለኞች በሚጠየቁበት ፍርድ ቤት እውነት እውነትነቷን እስካልሳተች ድረስ ጊዜው ይረዝም ይሆናል እንጂ ፍርዳችሁን እንደምታገኙና በሰፈራችሁበት ቁና መሰፈራችሁ እንደማይቀር ቅንጣት ጥርጣሬ የለኝም።

ለዚህም ከፍተኛ ወንጀል ቅጣት አይቀሬነት በዓለም አቀፍ ደረጃ ሰብአዊና ቁሳዊ ውድመትን ያደረሱ ድርጅቶችና የዘር ማጥፋት ተዋንያን የነበሩና የሆኑ ወንጀለኞችን ከናዚ ጀርመኑ ጁስታፖ ጀምሮ የዩጎዝላቪያው ኮሶቮ (ስሎቮዳን ሚሎሶቪችን) እንዲሁም የሩዋንዳውን የሁቱ እና ቱትሲ የዘር ማጥፋት ወንጀል በመከታተልና በዓለማቀፍ ሕግ ፊት በማቅረብ ፍትሕ በሚገባው ልክ ይበየን ዘንድ የተጉና በመትጋት ላይ ያሉ አካላት ሁሉ ሊመሰገኑ ይገባቸዋል። በእነሽመልሽ አብዲሳ መሪነት በአማራ እና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ላይ እየተፈፀመ ያለውን ጅምላ ጭፍጨፋም በተመሳሳይ ማጋለጥ ያስፈልጋል። ዛሬ በአድርባይነት ዝም ብንል ነገ ታሪክ ያወጣዋል። ዓለም ዓቀፍ የሕግ ምሁራን፣ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች፣ በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያ ወዳጆች ሁሉ በዚህ ጉዳይ ላይ ጠንክረው ሊሠሩ ይገባል። የበኩሌን ለመወጣት ጥሪዬን እንካችሁ እያልኩ በተከታዩ የስንኝ ቋጠሮ ልሰናበት።

## ካባ ልበስ

ምንድነው ልብስ- ምንድን ነው?፣

ቁማሩ እንደሁ የመሰሎችህም ነው- ልበስ ምንድን ነው?

ካባ ልበስ እንዲህ ነው- ልበስ እንዲህ ነው፣

የሰው ሕይዎት ምንህ ነው! ልበስ ምንድን ነው።

ካባ ልበስ በሞቴ- ልበስ በሞቴ፣

ካባ ልበስ በጓዳ- ልበስ በጓዳ፣

የኢሬቻ ልጅ! የአባ ገዳ! ልበስ በጓዳ።

# ፖለቲካና ሴትነት



ምዕራፍ ይመር

ዘመናዊው የሃገራችን ፖለቲካ የቅርብ ጊዜ ልምምዳችን ውጤት ነው። ግፋ ቢል፣ የሃምሳ እና ስድሳ ዓመታት ዕድሜ አካብቷል። የግራ ዘመም የፖለቲካ ሃቲት በናኘበት ዘመን፣ በርካቶች ወደ ተለያዩ ድርጅቶች ሲጎርፉ ነበር። በዋናነት ወጣቱ የህብረ-ተሰብ ክፍል ተጠቃሽ ሲሆን፣ አናሳውን ቁጥር ግን ይዘው የሚገኙት ሴቶች ናቸው። በፊቱንም፣ በተወሰነ መጠን ሴቶች ከሰርክ የአደባባይ እንቅስቃሴ የተገለሉ ቢሆንም፣ በፖለቲካው መስክ ግን እጅጉኑ በባሰ መልኩ ሴቶች ተገልለዋል እንጂ ዋናውን የአንበሳ ድርሻ ይዘው የተራመዱበት ጊዜ ጥቂት ነው።

ለዚህ ችግር ምክንያቶቹ ቢቆጠሩ አያልቁም። ሆኖም በጥቅሉ ሲዘረዘሩ ሁለት ናቸው።

አንደኛው ምክንያት በአብዛኛው ወገን ስለሴት ልጅ የተንሰራፋው አነስተኛ ግምት ነው። እንደሚታወቀው ፖለቲካው ሲዳሰስ፣ ጎልቶ የሚታየው የወንዶች ዓለም ነው። ቁልፍ የአመራር ስፍራዎች ወንዶች ተቆጣጥረው ይዘውታል። ነገር ግን ሴቶች ወደፊት እንዲመጡ፣ ከፊት ሆኖ የሚጠርግ አካል እምብዛም ነው። ምክንያቱም ሴት ልጅ የፖለቲካውን ዳገት እና ቁልቁለት ለመቋቋም አቅሙ ‹የላትም› ተብሎ ስለሚታሰብ ነው። ስለዚህም ሴት ፖለቲከኛ ከከፍተኛ የአመራር እርከን ውጭ ትደረጋለች። እንዲሁም በየደረጃው የሚያጋጥማት ጾታዊ ትንኮሳ ከመበራከቱ የተነሳ ከፖለቲካው ሙሉ በሙሉ ልትርቅ ትችላለች። ይህም ትልቅ አቅም እና ዕውቀት ያላት ሴት ከወሳኙ የፖለቲካ ስፍራ ስትርቅ የሚፈጠረው ክፍተት ከባድ ብቻ ሳይሆን አስጨናቂም ጭምር ነው።

ሁለተኛው ደግሞ ለሴቶች መብት የሚቆረቆሩ እና አቅማቸው ለማሳደግ የሚጥሩ ተቋማት ደካማ መሆን ነው። ማለትም የሴቶችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ ለማጎልበት የሚረዱ መንግስታዊም ሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ዓላማቸውን ማስፈጸም አቅቷቸዋል። አንድም በፋይናንስ ዕጥረት፣ ሁለቱም በሰው ሃብት ዕጥረት ምክንያት ያሰቡትን ያህል አልተራመዱም። ባሉበት እየረገጡ ይገኛሉ።

ለእነዚህ ችግሮች ሁነኛው መፍትሔ አንድ ነው። ይኸውም፣ ተቋማቱ ጠንክረው እንዲሰሩ ሰፊ ዕድል ማመቻቸት፣ ብሎም ለአቅም ግንባታ የሚያግዙ ግብዓቶችን በሰፊው እንዲያዳርሱ መንገዱን ማደላደል ነው። የእነዚህ ተቋማት የትኩረት ማዕከላት ሴቶች ናቸው። ሴቶችን ሳያሳትፉ፣ አንድም ጋት መራመድ አይችሉም። በመሆኑም፣ ተቋማቱ የሴቶችን የፖለቲካ ንቃተ-ህሊና ለማሳደግ ሲጥሩ፣ በአኳያው ደግሞ የፖለቲካ ድርጅቶች ሴቶች ወደ ፖለቲካ እንዲገቡ ማበረታታት ይኖርባቸዋል። በተለይ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች ሃላፊነታቸውን በሚገባ መወጣት ግድ ይላቸዋል። ይሁን እንጂ ከተለመደው የአዙሪት መንገድ ወጣ ተብሎ ካልታሰበ፣ አሁንም በርካታ ሴት ፖለቲከኞችን በሙሉ አቅማቸው ላንመለከታቸው እንችላለን፤ ▸





ኢትዮጵያ ዳግም
የህሊና እስረኞች
ቤት እንድትሆን
መፍቀድ የለብንም!

ባልደራስ
ለእውነተኛ ዲሞክራሲ

